የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

# ፌዴራል ነጋሪት ጋዜጣ

# FEDERAL NEGARIT GAZETA

OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA

አሥራ ሁለተኛ ዓመት ቁጥር ፩
አዲስ አበባ ህዳር ፰ ቀን ፲፱፻፺፰

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ

12th Year No. 1ADDIS
ABABA 17th November, 2005

**ማውጫ**

አዋጅ ቁጥር ፬፻፸፩/፲፱፻፺፰ ዓ.ም

የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ አስፈጻሚ አካላትን ሥልጣንና ተግባር ለመወሰን የወጣ አዋጅ……. ገጽ ፫ሺ፪፻፸፮

CONTENTS

Proclamation No.471 /2005

Definition of Powers and Duties of the Executive Organs of the Federal Democratic Republic of Ethiopia Proclamation …. Page 3276

## አዋጅ ቁጥር ፬፻፸፩ /፲፱፻፺፰

### የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ አስፈጻሚ አካላትን ሥልጣንና ተግባር ለመወሰን የወጣ አዋጅ

የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ አስፈጻሚ አካላትን አደረጃጀት፣ ሥልጣንና ተግባር እንደገና መወሰን አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ፤

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ መንግሥት አንቀጽ ፶፭/፩/ መሠረት የሚከተለው ታውጇል::

### ክፍል አንድ
### ጠ ቅ ላ ላ

**፩. አጭር ርዕስ**

ይህ አዋጅ “የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ አስፈጻሚ አካላትን ሥልጣንና ተግባር ለመወሰን የወጣ አዋጅ ቁጥር ፬፻፸፩/፲፱፻፺፰” ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል::

**፪. ትርጓሜ**

በዚህ አዋጅ ውስጥ የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር “ክልል” ማለት በሕገ መንግሥቱ አንቀጽ ፵፯ የተመለከተው ማንኛውም ክልል ሲሆን የአዲስ አበባና የድሬዳዋ ከተሞች አስተዳደሮችን ይጨምራል::

## PROCLAMATION NO. 471/2005.

### A PROCLAMATION TO PROVIDE FOR THE DEFINITION OF POWERS AND DUTIES OF THE EXECUTIVE ORGANS OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA

**WHEREAS**, it is found necessary to redefine the organization, powers and duties of the Executive Organs of the Federal Democratic Republic of Ethiopia;

**NOW, THEREFORE,** in accordance with Article 55 (1) of the Constitution, of the Federal Democratic Republic of Ethiopia, it is hereby proclaimed as follows:

### PART ONE
### GENERAL

**1. Short Title**

This Proclamation may be cited as the “Definition of Powers and Duties of the Executive Organs of the Federal Democratic Republic of Ethiopia Proclamation No. 471/2005.”

**2. Definitions**

In this Proclamation unless the context requires otherwise “Regional State” means any State referred to under Article 47 of the Constitution and includes the Addis Ababa and Dire Dawa city administrations.

## ክፍል ሁለት
## ስለጠቅላይ ሚኒስትሩ፣ ስለ ምክትል ጠቅላይ ሚኒስትሩና ስለሚኒስትሮች ምክር ቤት

### ፫. ስለጠቅላይ ሚኒስትሩ ሥልጣንና ተግባር

የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ጠቅላይ ሚኒስትር ሥልጣንና ተግባር በሕገ መንግሥቱ አንቀጽ ፸፬ የተመለከተው ይሆናል፡፡

### ፬. ስለምክትል ጠቅላይ ሚኒስትሩ ሥልጣንና ተግባር

የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ምክትል ጠቅላይ ሚኒስትር ሥልጣንና ተግባር በሕገ መንግሥቱ አንቀጽ ፸፭ የተመለከተው ይሆናል፡፡

### ፭. ስለሚኒስትሮች ምክር ቤት ሥልጣንና ተግባር

የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ሥልጣንና ተግባር በሕገ መንግሥቱ አንቀጽ ፸፯ የተመለከተው ይሆናል፡፡

### ፮. የሚኒስትሮች ምክር ቤት አባላት

፩/ የሚኒስትሮች ምክር ቤት የሚከተሉት አባላት ይኖሩታል፤

- ሀ) ጠቅላይ ሚኒስትር፤
- ለ) ምክትል ጠቅላይ ሚኒስትር፤
- ሐ) በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፱ የተመለከቱትን ሚኒስቴሮች የሚመሩ ሚኒስትሮች
- መ) በጠቅላይ ሚኒስትሩ የሚሰየሙ ሌሎች ባለሥልጣኖች፡፡

፪/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ ፩ /ሐ/ የተመለከተው ማንኛውም ሚኒስትር በምክር ቤቱ ስብሰባ ላይ ሊገኝ በማይችልበት ጊዜ በተለይ ካልወከለ በስተቀር በሹመት ቅድሚያ ያለው ሚኒስትር ዴኤታ ወይም ምክትል ሚኒስትር በምክር ቤቱ ስብሰባ ላይ ይሳተፋል፡፡

### ፯. የሚኒስትሮች ምክር ቤት አባላት የስብሰባ ሥነ ሥርዓት

፩/ የሚኒስትሮች ምክር ቤት፣

- ሀ) የራሱ የውስጥ ደንብ ይኖረዋል፤
- ለ) በውስጥ ደንቡ በሚወሰነው መሠረት መደበኛና አስቸኳይ ስብሰባዎች ያደርጋል፤
- ሐ) ምልአተ ጉባኤ የሚኖረው ከአባሎቹ ከግማሽ በላይ ሲገኙ ይሆናል፤

## PART TWO
## THE PRIME MINISTER, THE DEPUTY PRIME MINISTER AND THE COUNCIL OF MINISTERS

### 3. Powers and Duties of the Prime Minister

The powers and duties of the Prime Minister of the Federal Democratic Republic of Ethiopia shall be as specified under Article 74 of the Constitution.

### 4. Powers and Duties of the Deputy Prime Minister

The powers and duties of the Deputy Prime Minister of the Federal Democratic Republic of Ethiopia shall be as specified under Article 75 of the Constitution.

### 5. Powers and Duties of the Council of Ministers

The powers and duties of the Council of Ministers of the Federal Democratic Republic of Ethiopia shall be as specified under Article 77 of the Constitution.

### 6. Members of the Council of Ministers

1/ The Council of Ministers shall have the following members:

- a) the Prime Minister;
- b) the Deputy Prime Minister,
- c) Ministers heading the ministries specified under article 9 hereunder;
- d) other officials to be designated by the Prime Minister.

2/ Where any minister referred to in Sub-Article 1(c) of this Article cannot attend the meeting of the Council,. the senior minister of state or the vice minister of the ministry shall, unless specific delegation has been given, take part in the meeting of the Council.

### 7. Meeting Procedure of the Council of Ministers

1/ The Council of Ministers shall:

- a) have its own rules of procedure;
- b) conduct ordinary and extraordinary meetings in accordance with its rules of procedure;
- c) have a quorum where more than half of its members are present;

መ) የሚያስተላልፈው ውሣኔ በተባበረ ድምጽ ይሆናል፤ በተባበረ ድምጽ መወሰን ካልተ ቻለ በድምጽ ብልጫ ይወሰናል፡፡

፪/ ጠቅላይ ሚኒስትሩ፣

ሀ) የሚኒስትሮች ምክር ቤት አባላት አጀንዳ የማስያዝ መብታቸው እንደተጠበቀ ሆኖ፣ ለምክር ቤቱ በአጀንዳ የሚቀርቡ ጉዳዮችን ይወስናል፤

ለ) የምክር ቤቱን ስብሰባ ይመራል፤

ሐ) ለምክር ቤቱ በአጀንዳ የቀረበ ጉዳይ በሚመለከተው የምክር ቤቱ ኮሚቴ መታየት የሚያስፈልገው ሆኖ ካገኘው ስብሰባውን ለሌላ ጊዜ ያስተላልፋል፡፡

፫/ ጠቅላይ ሚኒስትሩ በማይኖርበት ጊዜ ምክትል ጠቅላይ ሚኒስትሩ የምክር ቤቱን ስብሰባ ይመራል፡፡

## ፰. የምክር ቤቱ ቋሚ ኮሚቴዎች

፩/ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ሥልጣንና ተግባሩን ለመወጣት ይረዳው ዘንድ የምክር ቤቱ አባላት የሚገኙባቸው ልዩ ልዩ ቋሚ ኮሚቴዎች ሊኖሩት ይችላል፡፡

፪/ የቋሚ ኮሚቴዎች ሥልጣንና ተግባር በምክር ቤቱ የውስጥ ደንብ ይወሰናል፡፡

## ክፍል ሦስት
## ስለሚኒስቴሮች

## ፱. መቋቋም

የሚከተሉት ሚኒስቴሮች በዚህ አዋጅ ተቋቁመዋል፤

፩/ የአቅም ግንባታ ሚኒስቴር፤
፪/ የትምህርት ሚኒስቴር፤
፫/ የንግድና ኢንዱስትሪ ሚኒስቴር፤
፬/ የግብርናና ገጠር ልማት ሚኒስቴር፤
፭/ የትራንስፖርትና መገናኛ ሚኒስቴር፤
፮/ የሥራና ከተማ ልማት ሚኒስቴር፤
፯/ የገንዘብና የኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር፤
፰/ የገቢዎች ሚኒስቴር፤
፱/ የፌዴራል ጉዳዮች ሚኒስቴር፤
፲/ የጤና ጥበቃ ሚኒስቴር፤
፲፩/ የፍትሕ ሚኒስቴር፤
፲፪/ የአገር መከላከያ ሚኒስቴር፤
፲፫/ የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር፤

d) pass decisions by consensus or, failing that, by majority vote.

2/ The Prime Minister shall

a) without prejudice to the rights of the members of the Council of Ministers to propose agenda items, determine the agenda of the Council:

b) preside over the meetings of the Council;

c) adjourn the meetings of the Council under circumstances where he finds it necessary to refer a case, included in the Council's agenda, to the relevant committee of the Council;

3/ In the absence of the Prime Minister, the Deputy Prime Minister shall preside over the meetings of the Council.

## 8. Standing Committees of the Council

1/ The Council of Ministers may, with a view to exercising its powers and duties, have various standing committees comprising of its members.

2/ The powers and duties of standing committees shall be defined in the manuals of the Council.

## PART THREE
## MINISTRIES

## 9. Establishment

The following Ministries are hereby established:

1/ the Ministry of Capacity Building;
2/ the Ministry of Education;
3/ the Ministry of Trade and Industry;
4/ the Ministry of Agriculture and Rural Development
5/ the Ministry of Transport and Communicationsns;
6/ the Ministry of Works and Urban Developments;
7/ the Ministry of Finance and Economic Development;
8/ the Ministry of Revenue;
9/ the Ministry of Federal Affairs;
10/ the Ministry of Health;
11/ the Ministry of Justice;
12/ the Ministry of National Defense;
13/ the Ministry of Foreign Affairs;

፲፬/ የማስታወቂያ ሚኒስቴር፤
፲፭/ የውሃ ሀብት ሚኒስቴር፤
፲፮/ የወጣቶችና ስፖርት ሚኒስቴር፤
፲፯/ የሴቶች ጉዳይ ሚኒስቴር፤
፲፰/ የባህልና ቱሪዝም ሚኒስቴር፤
፲፱/ የማዕድንና ኢነርጂ ሚኒስቴር፤
፳/ የሠራተኛና ማኅበራዊ ጉዳይ ሚኒስቴር፤

## ፲. <u>የሚኒስቴሮች የወል ሥልጣንና ተግባር</u>

እያንዳንዱ ሚኒስቴር፣

፩/ በሥራው መስክ፣

ሀ) ፖሊሲዎችንና ሕጎችን ያመነጫል፣ ዕቅድና በጀት ያዘጋጃል፣ ሲፈቀድም በሥራ ላይ ያውላል፤
ለ) የፌደራል መንግሥቱ ሕጎች በሥራ ላይ መዋላቸውን ያረጋግጣል፤
ሐ) የጥናትና ምርምር ተግባሮችን ያከናውናል፤ መረጃዎችን ይሰበስባል፣ ያቀነባብራል፣ ያሰራጫል፤
መ) ለክልሎች እንዳስፈላጊነቱ ድጋፍና ምክር ይሰጣል፤
ሠ) በሕግ መሠረት ውሎችንና ዓለም አቀፍ ስምምነቶችን ያደርጋል፤

፪/ በማቋቋሚያ ሕጎቻቸው ወይም በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፴፫ ተጠሪ የተደረጉለትን አስፈጻሚ አካላት አፈጻጸም በበላይነት ይመራል፣ ያስተባብራል፤ አደረጃጀቶቻቸውን እንዲሁም የሥራ ፕሮግራሞቻቸውን መርምሮ ለሚመለከተው የመንግሥት አካል እንዲቀርቡ ይወስናል፤

፫/ ተጠሪ የተደረጉለትን የመንግሥት የልማት ድርጅቶች በመንግሥት የልማት ድርጅቶች አዋጅ ቁጥር ፳፭/፲፱፻፹፬ መሠረት ይቆጣጠራል፣ የልማት አጋዥ ሆነው መሥራታቸውንም ያረጋግጣል፤

፬/ በዚህ አዋጅና በሌሎች ሕጎች የተሰጡትን ሥልጣንና ተግባሮች በሥራ ላይ ያውላል፤

፭/ ስለሥራው ክንዋኔ በየወቅቱ ለጠቅላይ ሚኒስትሩና ለሚኒስትሮች ምክር ቤት ሪፖርት ያቀርባል፡፡

## ፲፩. <u>የሚኒስትሮች ተጠሪነትና ኃላፊነት</u>

እያንዳንዱ ሚኒስትር፣

፩/ ተጠሪነቱ ለጠቅላይ ሚኒስትሩና ለሚኒስትሮች ምክር ቤት ይሆናል፤

14/ the Ministry of Information;
15/ the Ministry of Water Resources;
16/ the Ministry of Youth and Sports;
17/ the Ministry of Women's Affairs;
18/ the Ministry of Culture and Tourism;
19/ the Ministry of Mines and Energy;
20/ the Ministry of Labour and Social Affairs.

## 10. Common Powers and Duties of Ministries

Each Ministry shall:

1/ in its field of activity;

a) initiate policies and laws, prepare plans and budgets, and upon approval implement same:
b) ensure the enforcement of federal laws;
c) undertake study and research; collect, compile and disseminate information;
d) provide assistance and advice to Regional States, as necessary;
e) enter into contracts and international agreements in accordance with the law;

2/ direct and coordinate the performances of the executive organs made accountable to it under the laws establishing them or under Article 33 of this Proclamation; review the organizational structures as well as the work programs and budgets of the executive organs and approve their submission to the appropriate government organs;

3/ supervise the public enterprises, made accountable to it, in accordance with the Public Enterprises Proclamation No. 25/1992, and ensure that they operate as development catalysts;

4/ exercise the powers and duties given to it under this Proclamation and other laws;

5/ submit periodic performance reports to the Prime Minister and the Council of Ministers.

## 11. Accountability and Responsibility of Ministers

Each Minister shall:

1/ be accountable to the Prime Minister and the Council of Ministers;

፪/ የሚመራውን ሚኒስቴር ይወክላል፣ ሥልጣንና ተግባሩን ሥራ ላይ ያውላል፤

፫/ ለሚኒስቴሩ በተፈቀደው በጀትና የሥራ ፕሮግራም መሠረት ገንዘብ ወጪ ያደርጋል፤

፬/ በሚኒስቴሩ ውስጥ የአፈጻጸም አመራር ሥርዓት ተግባራዊ መደረጉን ያረጋግጣል።

፲፪. የሚኒስትር ዴኤታዎችና የምክትል ሚኒስትሮች ተጠሪነትና ኃላፊነት

፩/ የእያንዳንዱ ሚኒስቴር ሚኒስትር ዴኤታ ወይም ምክትል ሚኒስቴር ተጠሪነቱ ለሚኒስትሩ ሆኖ ተለይተው የሚሰጡትን ተግባሮች ያከናውናል።

፪/ ሚኒስትሩ በማይኖርበት ጊዜ በተለይ ካልወከለ በስተቀር በሹመት ቅድሚያ ያለው ሚኒስትር ዴኤታ ወይም ምክትል ሚኒስትር ተክቶት ይሰራል።

፲፫. የአቅም ግንባታ ሚኒስቴር

የአቅም ግንባታ ሚኒስቴር የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባሮች ይኖሩታል፤

፩/ የአገሪቱን የረጅም ጊዜ የልማት አቅጣጫ መሰረት በማድረግ በየጊዜው የሚታዩ የአቅም ክፍተቶችን በማጥናት ይለያል፤

፪/ አስፈላጊ የማሻሻያ ፕሮግራሞችና ፕሮጀክቶች በተቀናጀ ሁኔታ መቀረጻቸውንና መተግበራቸውን ያረጋግጣል፤

፫/ ልዩ ልዩ የማሻሻያ ፕሮግራሞችን ውጤታማ ለማድረግ የሚያስችል አጠቃላይ የክትትልና የግምገማ ሥርዓት ይዘረጋል፤

፬/ የአቅም መገንቢያ አቅሞች እንዲገነቡና በሚገባ ጥቅም ላይ እንዲውሉ ያደርጋል፤

፭/ በፌዴራል ሲቪል ሰርቪሱ ውስጥ ዘመናዊና የተሟላ የሰው ሀብት አመራር ሥርዓት መዘርጋቱንና በተግባር ላይ መዋሉን ያረጋግጣል፤

፮/ የኢንፎርሜሽንና ኮሙኒኬሽን ቴክኖሎጂ አጠቃቀም የሚስፋፋበትና የሚጠናከርበት ሁኔታ መመቻቸቱን ያረጋግጣል።

2/ represent and exercise the powers and duties of the Ministry he is heading;

3/ effect payments in accordance with the budget and work programs approved for the ministry;

4/ ensure the implementation of performance management system within the ministry.

**12. Accountability and Responsibility of Ministers of State and Vice Ministers.**

1/ Each minister of state or vice minister of a ministry shall be accountable to the minister and shall carry out the responsibilities specifically entrusted to him.

2/ The senior minister of state or vice minister of a ministry shall, unless the minister has given specific delegation, act on behalf of the minister in his absence.

**13. The Ministry of Capacity Building**

The Ministry of Capacity Building shall have the powers and duties to:

1/ undertake studies, on the basis of the country's long term development directions, to identify capacity gaps that may be observed from time to time;

2/ ensure the integrated formulation and coordinated implementation of the necessary reform programs and projects;

3/ establish a general monitoring and evaluation system to ensure the effectiveness of various reform programs;

4/ cause the creation and optimum utilization of capacity building capabilities;

5/ ensure the establishment and proper implementation of modern and comprehensive system for human resource management within the federal civil service;

6/ ensure the creation of conducive conditions for expanded and strengthened utilization of information and communication technology.

## ፲፬. የትምህርት ሚኒስቴር

የትምህርት ሚኒስቴር የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባሮች ይኖሩታል፤

፩/ የትምህርትና ሥልጠና ስታንዳርድ ያወጣል፤ ሥራ ላይ መዋሉንም ያረጋግጣል፤

፪/ የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ /፩/ አጠቃላይ አነጋገር እንደተጠበቀ ሆኖ፣

ሀ) አጠቃላይ የሥርዓተ ትምህርት ማእቀፍ ያዘጋጃል፤

ለ) ለአንደኛና ሁለተኛ ደረጃ መምህራን አነስተኛውን የትምህርት ብቃት መለኪያ ያወጣል፤

ሐ) በሙያና ቴክኒክ ዘርፍ የሙያ ሥልጠና ደረጃና የብቃት ማረጋገጫ ደረጃ ያወጣል፤

መ) የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ሊያሟሉ የሚገባቸውን አነስተኛውን ደረጃ ያወጣል፤

፫/ የከፍተኛ ትምህርት ተቋማትን ያቋቁማል፣ ያስፋፋል፣ እውቅና ይሰጣል፤ ጥራትና አግባብነት ያለው ትምህርት መስጠታቸውን ይቆጣጠራል፤

፬/ ትምህርትና ሥልጠናን በተመለከተ አገራዊ የአሕዝቦት ተግባሮችን ያከናውናል፡፡

## ፲፭. የንግድና ኢንዱስትሪ ሚኒስቴር

የንግድና ኢንዱስትሪ ሚኒስቴር የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባሮች ይኖሩታል፤

፩/ ንግድ፣ ኢንዱስትሪና ኢንቨስትመንት እንዲስፋፋ ያደርጋል፤

፪/ የአገሪቱ የወጪ ንግድ የሚስፋፋበትንና የሚጠናከርበትን ሁኔታ ያመቻቻል፤

፫/ የአገሪቱን የውጭ ንግድ ግንኙነቶች ያጠናክራል፤ የንግድ ፣ የወደብና የትራንዚት አገልግሎት ስምምነቶችን ይደራደራል፣ ያስፈጽማል፤

፬/ የአገር ውስጥ ንግድን ለማስፋፋትና ለማጠናከር ቀልጣፋ የግብይት ሥርዓትና ተገቢ የንግድ አሠራር እንዲሰፍን ያደርጋል፤

፭/ አግባብ ባላቸው ሕጎች መሠረት የንግድ ምዝገባና ፈቃድ አገልግሎቶችን ይሰጣል፣ ይቆጣጠራል፤

## 14. The Ministry of Education

The Ministry of Education shall have the powers and duties to:

1/ set education and training standards, and ensure the implementation of same;

2/ without prejudice to the generality of Sub-Article (1) of this Article,

a) formulate a general framework of curricula for education;

b) set minimum educational qualification requirements for primary and secondary school teachers;

c) set standards for vocational and technical training and certification;

d) set minimum standards for higher education institution.

3/ establish, expand and accredit higher education institutions; and ensure that they offer quality and relevant education;

4/ undertake national popularization programs on education and training.

## 15. The Ministry of Trade and Industry

The Ministry of Trade and Industry shall have the powers and duties to:

1/ promote the expansion of trade, industry and investment;

2/ create conducive conditions for the promotion and development of the country's export trade;

3/ strengthen the country's foreign trade relations and negotiate and implement trade, port and transit agreements;

4/ maintain efficient marketing systems and fair trade practices to promote and develop domestic trade;

5/ provide business registration and licensing services and regulate same in accordance with the relevant laws;

፮/ የዋጋ ቁጥጥር ሊደረግባቸው የሚገቡ መሠረታዊ የንግድ ዕቃዎችንና አገልግሎቶችን ዋጋ እያጠና ለሚኒስትሮች ምክር ቤት ያቀርባል ሲፈቀዱም ተግባራዊነታቸውን ይከታተላል፤

፯/ የኢንዱስትሪ ልማትን ለማፋጠን የሚያስችሉ የተመቻቹ ሁኔታዎች እንዲፈጠሩ ያደርጋል፤

፰/ ስትራቴጂያዊ ትኩረት ለሚሰጣቸው ኢንዱስትሪዎች ድጋፍ ይሰጣል፤

፱/ የጥቃቅንና የአነስተኛ ንግድ ሥራዎች ልማት እንዲስፋፋ ያደርጋል፤

፲/ የመንግሥት የልማት ድርጅቶች እንዲጠናከሩና ወደ ግል ይዞታ እንዲዛወሩ ያደርጋል፤

፲፩/ የጥራትና ደረጃዎች ምደባ አገልግሎት በአግባቡ እንዲሰጥ መደረጉን ያረጋግጣል፤

፲፪/ የንግድና የዘርፍ ማኅበራት ምክር ቤቶች እንዲሁም በኢንዱስትሪ መስክ የሚደራጁ የሙያ ማኅበራት እንዲቋቋሙ ያበረታታል፣ የተቋቋሙትንም እንዲጠናከሩ ያደርጋል፤

፲፫/ ለአገር ውስጥና ለውጭ ኢንቨስትመንት ምቹ ሁኔታዎችን ይፈጥራል፤

፲፬/ ለኢንቨስተሮች የተቀላጠፈ አገልግሎት ለመስጠት እንዲቻል ሁሉም አገልግሎቶች በአንድ ማዕከል የሚሰጡበትን ሁኔታ ያመቻቻል።

## ፲፮. የግብርናና ገጠር ልማት ሚኒስቴር

፩/ የግብርናና ገጠር ልማት ሚኒስቴር የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባሮች ይኖሩታል፤

ሀ) የግብርናውን ዘርፍ ምርታማነት ለማሻሻል ለአርሶ አደሩና ለአርብቶ አደሩ እንዲሁም ለግል ባለሃብቱ የሚሰጡ የኤክስቴንሽንና የሥልጠና አገልግሎቶች እንዲስፋፉ ያደርጋል፤

ለ) ወደ ሀገር በሚገቡትም ሆነ ከሀገር በሚወጡት ዕጽዋት፣ አዝርዕት፣ እንስሳትና የእንስሳት ተዋጽኦ ላይ የኳራንቲን ቁጥጥር ያደርጋል፤

ሐ) የእንስሳትና የዕጽዋት በሽታዎች ወረርሽኝንና ተዛማች ተባዮችን ይከላከላል፤

6/ undertake and submit to the Council of Ministers price studies relating to basic commodities and services that have to be under price control and, upon approval, follow up the implementation of same;

7/ create conducive conditions for the acceleration of industrial development;

8/ provide support to industries considered to be of strategic importance;

9/ promote the expansion of micro and small enterprises;

10/ ensure the strengthening and privatization of public enterprises;

11/ ensure the proper provision of quality and standardization service;

12/ encourage the establishment of chambers of commerce and sectoral associations as well as professional associations in the industrial sector and strengthen those already existing;

13/ create enabling environment for domestic and foreign investment;

14/ facilitate the provision of efficient one-stop-shop service to investors.

## 16. The Ministry of Agriculture and Rural Development

1/ The Ministry of Agriculture and Rural Development shall have the powers and duties to:

a) promote the expansion extension and training services provided to peasants and pastoralists as well as private investors to improve the productivity of the agricultural sector;

b) conduct quarantine on plants, seeds, animals and animal products brought into and taken out of the country;

c) control the outbreak of animal and plant diseases and migratory pests;

መ) የተፈጥሮ ሀብት በዘላቂ የግብርና ልማት የሚጠበቅበትንና የሚለማበትን ስልት ይቀይሳል፣ ተግባራዊ የሚሆን በትን ሁኔታ ያመቻቻል፤

ሠ) የግብርና ግብዓት አቅርቦት፣ ሥርጭ ትና ግብይት አቅምን ይገነባል፣ አቅርቦቱን ያረጋግጣል፤

ረ) የግብርና ልማቱን ገበያ መር በማድረግ ለግብርና ምርቶች የወጪ ገበያን ለማረጋገጥ ተወዳዳሪ የግብይት ሥርዓት መፈጠሩን ያረጋግጣል፤

ሰ) የምግብ ዋስትና ፕሮግራም መተግበ ሩንና የአደጋ መከላከልና ዝግጁነት ሥራዎች በሚገባ እንዲከናወኑ መደረጋቸውን ያረጋግጣል፤

ሸ) ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመተባ በር የገጠር መሠረተ ልማት አገልግሎ ቶች እንዲስፋፉ ሁኔታዎችን ያመቻ ቻል፤

ቀ) የኅብረት ሥራ ማኅበራት የሚስፋፉበ ትና የብድር አገልግሎቶች ለአርሶአደ ሮችና ለአረብቶ አደሮች የሚቀርቡበት ሁኔታ መመቻቸቱን ያረጋግጣል፤

በ) በግብርና ምርት ላይ ተፅዕኖ የሚያስከትሉ ወቅታዊ ሁኔታዎችን ይከታተላል፤ የቅድሚያ ማስጠንቀቂያ ሥርዓት ይዘረጋል፤

ተ) የግብርና ልማትን ለማፋጠንና የገጠር ቴክኖሎጂን ለማሻሻል የሚረዱ የማሰ ልጠኛ ተቋሞችንና ማዕከሎችን ያቋቁ ማል፣ ይመራል፤

ቸ) የግብርና ምርምርና የብዝሀ ሕይወት ጥበቃ ሥራዎች በአግባቡ እንዲከናወኑ መደረጋቸውን ያረጋግጣል።

፪/ በሥራ ላይ ባሉ የሌሎች ሕጎች ድንጋጌዎች ለግብርና ሚኒስቴርና ለገጠር ልማት ሚኒስቴር ተሰጥተው የነበሩ ሥልጣንና ተግባሮች፣ ቡና ወደ ውጭ ለመላክ የሚያስችል የምስክር ወረቀት ስለመስጠት በአዋጅ ቁጥር ፩፻፲፮/፲፱፹፯ አንቀጽ ፭/፮/ ለቡናና ሻይ ባለሥልጣን ተሰጥተው የነበሩ ሥልጣንና ተግባሮች፣ በማዳበሪያ ማምረትና ንግድ አዋጅ ቁጥር ፩፻፴፯/፲፱፻፺፩፣ በዕፅዋት ዘር አዋጅ ቁጥር ፪፻፮/፲፱፻፺፪ እና በአዋጅ ቁጥር ፪፻፹፰/፲፱፻፺፬ አንቀጽ ፲፪ ለብሔራዊ የግብርና ግብዓት ባለሥልጣን ተሰጥተው የነበሩ ሥልጣንና ተግባሮች እንዲሁም በዕቃ ደረሰኝ ሥርዓት አዋጅ ቁጥር ፫፻፸፪/፲፱፻፺፮ ለንግድና ኢንዱስ ትሪ ሚኒስቴር ከተሰጠው ሥልጣንና ተግባር ውስጥ የግብርና ምርቶችን የሚመለከተው በዚህ አዋጅ ለግብርናና የገጠር ልማት ሚኒስቴር ተሰጥተዋል።

d) devise and facilitate the implementation of a strategy for natural resources protection through sustained agricultural development;

e) build capacity for the supply, distribution and marketing of agricultural inputs, and ensure the supply of same;

f) ensure the creation of export market for agricultural products through market led agricultural development and competitive marketing system;

g) ensure the implementation of the food security program and the proper carrying out of disaster prevention and preparedness activities;

h) in cooperation with the concerned organs, create conducive conditions for the expansion of rural development infrastructure;

i) ensure the creation of enabling environment for the expansion of cooperatives and the provision of credit facilities to peasants and pastoralists;

j) monitor events affecting agricultural production and set up an early warning system;

k) establish and direct training establishments that assist the acceleration of agricultural development and the improvement of rural technology;

l) ensure the proper carrying out of agricultural research and conservation of biodiversity.

2/ The powers and duties given to the Ministry of Agriculture and the Ministry of Rural Development by the provisions of other laws, currently in force, the powers and duties which were given to the Coffee and Tea Authority under Article 5(6) of Proclamation No. 116/1995 with regard to the issuance of coffee export authorization certificate, the powers and duties given to the National Agricultural Input Authority under the Fertilizer Manufacturing and Trade Proclamation No. 137/1998, the Seed Proclamation No. 206/2000 and Article 12 of Proclamation No. 288/2002 and the powers and duties vested in the Ministry of Trade and Industry under the Proclamation to Provide for a Warehouse Receipts System No. 372/2003 with respect to agricultural products are hereby given to the Ministry of Agriculture and Rural Development.

## ፲፯. የትራንስፖርትና መገናኛ ሚኒስቴር

የትራንስፖርትና መገናኛ ሚኒስቴር የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባሮች ይኖሩታል፤

፩/ የትራንስፖርትና የመገናኛ አገልግሎቶች እንዲስፋፉ ያደርጋል፤

፪/ የትራንስፖርትና የመገናኛ አገልግሎቶች አቅርቦት የሀገሪቱን የልማት ስትራቴጂ በተሟላ ሁኔታ እንዲያገለግልና የተመጣጠነ ክልላዊ ሥርጭት እንዲኖረው መደረጉን ያረጋግጣል፤

፫/ የትራንስፖርትና የመገናኛ አገልግሎቶች አቅርቦት በተቀናጀ መንገድ እንዲፈጸም መደረጉን ያረጋግጣል፤

፬/ የትራንስፖርትና የመገናኛ አገልግሎቶች አስተማማኝነትና ደህንነታቸው የተጠበቀ መሆኑን ለማረጋገጥ የሚያስችል የቁጥጥር ሥርዓት እንዲዘረጋና ሥራ ላይ እንዲውል ያደርጋል፤

፭/ የባህርና የትራንዚት አገልግሎቶችን ይቆጣጠራል፤

፮/ የኢትዮ-ጅቡቲ ምድር ባቡር ድርጅትን የሥራ እንቅስቃሴዎች በሁለቱ አገሮች መካከል በተደረገው ስምምነት መሠረት ይከታተላል።

## ፲፰. የሥራና ከተማ ልማት ሚኒስቴር

፩/ የሥራና ከተማ ልማት ሚኒስቴር የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባሮች ይኖሩታል፤

ሀ) ለዲዛይንና ለኮንስትራክሽን ሥራዎች ደረጃ ያወጣል፣ ተግባራዊነታቸውን ይከታተላል፣ ይቆጣጠራል፤

ለ) በፌዴራል መንግሥት በጀት ለሚሠሩ የኮንስትራክሽን ሥራዎች ዲዛይኖችና የኮንስትራክሽን ሥራ ውሎች እንዲዘጋጁ ያደርጋል፤

ሐ) በፌዴራል መንግሥት የሚከናወን የኮንስትራክሽን ሥራ በተገባለት ውል መሠረት የጥራት ደረጃው፣ የጊዜና የዋጋ ገደቡ ተጠብቆ መሠራቱን ለማረጋገጥ የሚያስችል ቁጥጥር እንዲኖር ያደርጋል፣ በበላይነትም ይቆጣጠራል፤

**17. The Ministry of Transport and Communications**

The Ministry of Transport and Communications shall have the powers and duties to

1/ promote the expansion of transport and communication services;

2/ ensure that the provisions of transport and communication services are in line with the country's development strategy and meet the requirements of equitable regional distribution;

3/ ensure the integrated provision of transport and communication services;

4/ cause the formulation and implementation of regulatory frameworks to ensure the provision of reliable and safe transport and communication services;

5/ regulate maritime and transit services;

6/ follow up the activities of the Ethio-Djibouti Railways in accordance with the agreements concluded between the two countries.

**18. The Ministry of Works and Urban Development**

1/ The Ministry of Works and Urban Development shall have the powers and duties to:

a) set standards for design and construction works, and follow up and supervise the implementation of same;

b) ensure the preparation of designs and contract documents for construction works financed by the Federal Government;

c) cause the supervision of and inspect the execution of construction works financed by the Federal Government to ensure their conformity with the quality standards, time limits and cost as provided in their contracts;

መ) መሐንዲሶችንና አርክቴክቶችን ይመዘግባል፣ የሙያ ችሎታ ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት ይሰጣል፤ የሥራ ተቋራጮችንና የአማካሪዎችን ደረጃ ይወስናል፣ ከአንድ በላይ በሆኑ ክልሎች ውስጥ መሥራት ለሚችሉ የሥራ ተቋራጮችና አማካሪዎች የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት ይሰጣል፤

d) register and issue certificates of professional competence to engineers and architects; determine the grades of contractors and consultants, and issue certificates of competence to those operating in more than one Regional State;

ሠ) በአገር ውስጥ የሚመረቱ የኮንስትራክሽን ዕቃዎችን ዓይነትና ጥራት ለማሻሻል የሚረዳ ምርምር ያካሂዳል፤

e) undertake research for improving the types and qualities of local construction materials;

ረ) የፌዴራል መንገዶች በአግባቡ እንዲገነቡና ደህንነታቸው እንዲጠበቅ መደረጉን እንዲሁም የመንገድ ፈንድ በአግባቡ በጥቅም ላይ እንዲውል መደረጉን ያረጋግጣል፤

f) ensure the proper construction and maintenance of federal roads and the proper utilization of the road fund;

ሰ) አከታተምን በሚመለከት ጥናት ያካሂዳል፣ የከተሞችን ደረጃ መመዘኛ ያወጣል፤

g) undertake studies relating to urbanization, and set criteria for grading urban centers;

ሸ) የከተማ ነዋሪው ሕዝብ ከአቅሙ ጋር የተመጣጠነ መኖሪያ ቤት እንዲሠራ አጠቃላይ አቅጣጫ ለመቀየስ የሚያስችሉ ጥናቶችን ያካሂዳል፤ ለተግባራዊነታቸውም ለከተሞች የአቅም ግንባታ ድጋፍ ይሰጣል፤

h) undertake studies for setting general directions for urban dwellers to build dwelling houses compatible with their own means; provide capacity building support to urban centers for the implementation of same;

ቀ) የከተማ ልማት ሥራ ከድህነት ቅነሳ ጋር የተቀናጀ እንዲሆን ጥናቶችን ያካሂዳል፤ ለተግባራዊነታቸውም ድጋፍ ይሰጣል፤

i) undertake studies for the integration of urban development with poverty reduction activities, and support the implementation of same;

በ) ከተሞች የአካባቢያቸው የልማት ማዕከል እንዲሆኑ ሁለገብና የተቀናጀ ድጋፍ ይሰጣል፤

j) provide all-round and coordinated support to urban centers to make them development centers capable of influencing their surroundings;

ተ) ከተሞች የአገልግሎት አሰጣጣቸውን እንዲያሻሽሉ የአቅም ግንባታ እገዛ ያደርጋል፤ አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ በከተሞች ልማት መስክ የማሠልጠኛና የምርምር ተቋሞችን ያቋቁማል፤

k) provide capacity building support to urban centers for improving their service delivery; and where necessary, establish training and research institutions in the field of urban development;

ቸ) ከክልሎች ጋር በመተባበር የከተሞች ልማት ከገጠር ልማት ጋር በተቀናጀ መንገድ የሚከናወንበትን ሁኔታ በሚመለከት ጥናት ያደርጋል፤ ተግባራዊ እንዲሆን ያግዛል፤ አፈጻጸሙንም ይከታተላል፤

l) in cooperation with Regional States, undertake studies for the integration of urban and rural development activities; assist and follow up the implementation of same;

ኀ) ለፌዴራል መንግሥት ተጠሪ የሆኑ የከተማ አስተዳደሮችን የሥራ እንቅስቃሴዎች ይከታተላል፤

m) follow up the activities of the city administration accountable to the Federal Government;

ነ) ለሌላ የመንግሥት አካል በሕግ የተሰጠው ሥልጣን እንደተጠበቀ ሆኖ፣ በፌዴራል መንግሥት ባለቤትነት ሥር የሚገኙ ቤቶች አስተዳደር በአግባቡ እንዲከናወን መደረጉን ያረጋግጣል፤

ኘ) አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ ከሥልጣኑ በከፊል ለሌላ የፌዴራል መንግሥት አካል በውክልና መስጠት ይችላል።

፪/ በሥራ ላይ ባሉ የሌሎች ሕጎች ድንጋጌዎች የከተማ ልማት ዘርፍን በሚመለከት ለፌዴራል ጉዳዮች ሚኒስቴር ተሰጥተው የነበሩ ሥልጣንና ተግባሮች በዚህ አዋጅ ለሥራና ከተማ ልማት ሚኒስቴር ተሰጥተዋል።

## ፲፱. የገንዘብና የኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር

የገንዘብና የኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባሮች ይኖሩታል፤

፩/ የፌዴራል መንግሥቱን የልማት ዕቅድ አዘገጃጀት ሥርዓት ይዘረጋል፣ እቅዱንም የሚመለከታቸውን አካላት አስተባብሮ ያዘጋጃል፣ ተግባራዊነቱንም ይከታተላል፤

፪/ የፌዴራል መንግሥቱን የበጀት፣ የሂሳብ አያያዝ፣ የክፍያና የውስጥ ኦዲት ሥርዓት ይዘረጋል፣ በሥራ ላይ መዋሉን ይከታተላል፤

፫/ የፌዴራል መንግሥቱን በጀት ያዘጋጃል፣ አፈጻጸሙን ይከታተላል፤

፬/ የፌዴራል መንግሥቱን የግዥና የንብረት አስተዳደር ሥርዓት ይዘረጋል፣ በሥራ ላይ መዋሉን ይቆጣጠራል፤

፭/ የውጭ የልማት ዕርዳታና ብድር ያሰባስባል፣ ይደራደራል፣ ይፈርማል፣ አፈጻጸሙን ይከታተላል፤

፮/ የፌዴራል መንግሥትን የፋይናንስ ክንውንና የገንዘብ ይዞታ የሚያሳይ ጠቅላላ መግለጫ በየዓመቱና ባስፈለገ ጊዜ ለሚኒስትሮች ምክር ቤት ያቀርባል፤

፯/ በሌላ የፌዴራል መንግሥት አካል ይዞታ ሥር ያልዋለን የፌዴራል መንግሥት ንብረት ያስተዳድራል፤

n) without prejudice to the powers given by law to any other government organ, ensure the proper administration of houses owned by the Federal Government;

o) delegate part of its powers to other federal government organs as deemed necessary.

2/ The powers and duties given to the Ministry of Federal Affairs, with respect to urban development sector, by the provisions of other laws, currently in force, are hereby given to the Ministry of Works and Urban Development.

## 19. The Ministry of Finance and Economic Development

The Ministry of Finance and Economic Development shall have the powers and duties to:

1/ establish a system for the preparation of development plan of the Federal Government; prepare the plan in cooperation with concerned organs and follow up implementation of same;

2/ establish systems of budgeting, accounting, disbursement and internal audit for the Federal Government, and follow up implementation of same;

3/ prepare the Federal Government budget and follow up implementation of same;

4/ establish a system of procurement and property administration for the Federal Government, and supervise the implement ation of same;

5/ mobilize, negotiate and sign foreign development aid and loans, and follow up implementation of same;

6/ submit, annually and whenever necessary, to the Council of Ministers general reports on the financial performance and status of the Federal Government;

7/ administer property of the Federal Government which is under the possession of any other organ of the Federal Government;

፰/ የፌዴራል መንግሥት አክሲዮኖችን፣ የሚተላለፉና የማይተላለፉ የገንዘበ ሰነዶችንና ሌሎች ተመሳሳይ ተቀማጭ የገንዘብ ሀብቶችን ይይዛል፤ ይጠብቃል፤

፱/ የፌዴራል መንግሥትን የልማት ዕቅዶች አፈጻጸም ይገመግማል፤ የክልሎችን የልማት አፈጻጸም በጥቅሉ የሚያካትት ሀገራዊ የልማት ዕቅዶች አፈጻጸም ዓመታዊ ሪፖርት አዘጋጅቶ ለሚኒስትሮች ምክር ቤት ያቀርባል፤

፲/ የፌዴራሉ መንግሥት የሚተዳደርበትን በተለይም የታክስና የቀረጥ መሠረት የሆነ የፋይናንስ ፖሊሲ ያመነጫል፤

፲፩/ የአገሪቱን የሥነ ሕዝብ ፖሊሲ ያዘጋጃል፣ ሲፈቀድም አፈጻጸሙን ይከታተላል፣ ያስተባብራል፣ ይቆጣጠራል፤

፲፪/ የካርታና የማዕከላዊ ስታትስቲክስ ሥራዎች በአግባቡ እንዲከናወኑ መደረጋቸውን ያረጋግጣል፡፡

## ፳. የገቢዎች ሚኒስቴር

የገቢዎች ሚኒስቴር የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባሮች ይኖሩታል፤

፩/ ዘመናዊ የታክስ አስተዳደር ሥርዓት ይመሠርታል፣ በአግባቡ ተግባራዊ እንዲሆን መደረጉንም ያረጋግጣል፤

፪/ የገቢ ሰብሳቢ መሥሪያ ቤቶችን አፈጻጸም በማስተባበርና በመቆጣጠር የፌዴራል መንግሥት ገቢ በትክክልና በወቅቱ እንዲሰበሰብ ያደርጋል፤

፫/ ኢንቨስትመንትን ለማበረታታት ለባለሃብቶች የተሰጡ የታክስና ቀረጥ ነፃ መብቶችን ያስፈጽማል፤

፬/ ታክስ ከፋዩ ሕብረተሰብ ግዴታውን በፈቃደኝነት የመወጣት ባህልን ማዳበር የሚያስችሉት ትምህርታዊ ፕሮግራሞች እንዲቀረጹና ሥራ ላይ እንዲውሉ ያደርጋል፡፡

## ፳፩. የፌዴራል ጉዳዮች ሚኒስቴር

የፌዴራል ጉዳዮች ሚኒስቴር የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባሮች ይኖሩታል፤

፩/ የሕዝቡ ሰላም መጠበቁን በማረጋገጥ ረገድ አግባብ ካላቸው የፌዴራልና የክልል መንግሥት አካላት ጋር በመተባበር ይሰራል፤

8/ be the repository of and safeguard the Federal Government's shares, negotiable and non-negotiable instruments and other similar financial assets;

9/ evaluate the performance of development plans of the Federal Government; prepare and submit to the Council of Ministers annual national reports incorporating summarized reports of Regional States;

10/ initiate fiscal policy of the Federal Government that particularly serves as a basis for taxes and duties;

11/ formulate the population policy of the country and, upon approval follow up, co-ordinate and supervise its implementation;

12/ ensure the proper carrying out of activities relating to mapping and central statistics

## 20. The Ministry of Revenue

The Ministry of Revenue shall have the powers and duties to:

1/ establish and ensure the proper implementation of a modern tax administration system;

2/coordinate and supervise the performances of revenue collecting agencies for proper and timely collection of federal government revenue;

3/ enforce tax and duty exemption incentives given to investors;

4/ cause the preparation and implementation of educational programs designed to promote the culture of voluntary discharge of tax obligations.

## 21. The Ministry of Federal Affairs

The Ministry of Federal Affairs shall have the powers and duties to:

1/ cooperate with concerned federal and regional state organs in maintaining public order;

፪/ የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ መንግሥት አንቀጽ ፵፰ እና ፷፪/፮/ ድንጋጌዎች እንደተጠበቁ ሆነው፣ በክልሎች መካከል የሚነሱ አለመግባባቶች የሚፈቱባቸውን ሁኔታዎች ያመቻቻል፤

፫/ አግባብ ያላቸው ሕጎች እንደተጠበቁ ሆነው፣ ከክልሎች ጥያቄ ሲቀርብ በክልሎች ውስጥ የሚፈጠሩ አለመግባባቶችና ግጭቶች በዘላቂነት የሚፈቱበትን ፖለቲካዊ መፍትሔ ይቀይሳል፣ ተግባራዊ ያደርጋል፤

፬/ ፌዴራል መንግሥቱ በክልሎች ጉዳይ ጣልቃ እንዲገባ ሲወሰን አፈጻጸሙን ያስተባብራል፤

፭/ ለክልሎች በተለይም ለታዳጊ ክልሎች ልዩ ትኩረት በመስጠት ድጋፍ ያደርጋል፣

፮/ በፌዴራል መንግሥትና በክልሎች መካከል በመግባባትና በአጋርነት ላይ የተመሠረተ መልካም ግንኙነትና ትብብር እንዲኖር በማድረግ የፌዴራል ሥርዓቱ እንዲጠናከር የግንኙነቱ ማዕከል ሆኖ ያገለግላል፤

፯/ ሌሎች የፌዴራል መንግሥት አካላት ለታዳጊ ክልሎች የሚያደርጓቸውን ድጋፎች ያስተባብራል፣ ያቀናጃል፤

፰/ የፌዴራል ፖሊስ፣ የፌዴራል ማረሚያ ቤቶችና ፈንጂ የማምከን ሥራዎች በአግባቡ እንዲከናወኑ መደረጋቸውን ያረጋግጣል።

## ፳፪. የጤና ጥበቃ ሚኒስቴር

የጤና ጥበቃ ሚኒስቴር የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባሮች ይኖሩታል፤

፩/ የጤናውን ዘርፍ ልማት አገራዊ እንቅስቃሴ ያስተባብራል፣ ይመራል፤

፪/ ተላላፊና ተላላፊ ያልሆኑ በሽታዎችን ለመከላከልና ለማጥፋት የሚያስችሉ ስልቶችን ይቀይሳል፣ ተግባራዊነታቸውንም ይከታተላል፤

፫/ በምግብ እጥረት ወይም አለመመጣጠንና ብክለት ምክንያት የሚመጡ በሽታዎችን ለመከላከል የሚያግዙ ስልቶችን ይቀይሳል፣ ተግባራዊነታቸውን ይከታተላል፤ የምግቦችን ለጤና ተስማሚነት ያረጋግጣል፤

፬/ የሕዝቡን ጤና ለመጠበቅ አገሪቱን ከሌሎች አገሮች በሚያገናኙ ዋና ዋና የመግቢያና መውጫያ በሮች የኳራንቲን ቁጥጥር ያደርጋል፤

2/ without prejudice to the provisions of Article 48 and 62(6) of the Constitution of the Federal Democratic Republic of Ethiopia, facilitate the resolution of misunderstandings arising between Regional States;

3/ without prejudice to the provisions of the relevant laws and upon requests of Regional States, devise and implement sustainable political solutions for misunderstandings and conflicts that may arise within Regional States;

4/ coordinate the implementation of decisions authorizing the intervention of the Federal Government in the affairs of Regional States;

5/ provide assistance to Regional States particularly to the emerging ones;

6/ serve as a focal point in creating good federal-regional relationship and cooperation based on mutual understanding and partnership and thereby strengthen the federal system;

7/ coordinate and integrate supports of other federal organs to the emerging Regional States:

8/ ensure the proper carrying out of federal police, federal prisons and mine action activities.

## 22. The Ministry of Health

The Ministry of Health shall have the powers and duties to:

1/ coordinate and direct the country's health sector development program:

2/ devise and follow up the implementation of strategies for preventing and eradicating communicable and non-communicable diseases;

3/ devise and follow up the implementation of strategies for preventing malnutrition and food contamination; certify and supervise the safety of food stuffs;

4/ undertake the necessary quarantine at the main entry and exit points of the country to safeguard public health;

፭/ ለሕዝብ ጤና አስጊ ሁኔታዎች ሲፈጠሩና አደጋዎች ሲከሰቱ ተገቢውን እርምጃ ይወስዳል፣ የሌሎችንም እርምጃዎች ያስተባብራል፤

፮/ በአገሪቱ ውስጥ የአስፈላጊ መድኃኒቶችና የህክምና መሣሪያዎች በቂ አቅርቦት እንዲኖርና በአግባቡ ጥቅም ላይ እንዲውሉ ያደርጋል፤

፯/ የባህል መድሃኒቶች እንዲጠኑ፣ እንዲመዘገቡና ጥቅም ላይ እንዲውሉ ሁኔታዎችን ያመቻቻል፣ ባለሙያዎችም እንዲመዘገቡና ተገቢውን አገልግሎት እንዲሰጡ አስፈላጊውን ድጋፍ ያደርጋል፤

፰/ የጤና ምርምር ማዕከላት ያቋቁማል፣ ያስተዳድራል፤

፱/ የጤና አገልግሎቶች ሊኖራቸው የሚገባውን ደረጃ ይወስናል፣ አፈጻጸሙን ይቆጣጠራል፤

፲/ በሕዝብ ጤና አገልግሎቶች በልዩ ልዩ ደረጃ የሚሠማሩ ባለሙያዎችን የብቃት ደረጃ ይወስናል፣ የሙያ ብቃት ማረጋገጫ የምስክረ ወረቀት ይሰጣል፤

፲፩/ የመድኃኒት አስተዳደርና ቁጥጥር ሥራዎች እንዲከናወኑ መደረጋቸውን ያረጋግጣል፤

፲፪/ አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ ከሥልጣኑ በከፊል ለክልል ጤና ቢሮዎች ወይም ለሌሎች የመንግሥት አካላት በውክልና መስጠት ይችላል።

## ፳፫. የፍትሕ ሚኒስቴር

የፍትሕ ሚኒስቴር የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባሮች ይኖሩታል፤

፩/ የሕግ ጉዳዮችን በሚመለከት የፌዴራል መንግሥት ዋና አማካሪ ሆኖ ይሠራል፤

፪/ በፌዴራል ፍርድ ቤቶች ሥልጣን ሥር በሚወድቁ ወንጀሎች ፌዴራል መንግሥቱን በመወከል ይከራከራል፣

፫/ በፌዴራል ፍርድ ቤቶች ሥልጣን ሥር የሚወድቁ ወንጀል ተፈጽሟል ብሎ ሲያምን ምርመራ እንዲደረግ ያዛል፣ በቂ ምክንያት ሲኖር የተጀመረ ምርመራ እንዲቆም ወይም ተጨማሪ ምርመራ እንዲከናወን ያደርጋል፣ በሕግ መሠረት የወንጀል ክስ ያነሳል፤

5/ undertake appropriate measures in the events of disasters and other situations that threaten public health, and coordinate measures to be taken by other bodies;

6/ ensure the availability and proper utilization of essential drugs and medical equipment in the country;

7/ create conducive conditions for research, registration and utilization of traditional medicines; and give the necessary support to practitioners to register and practice their profession;

8/ establish and administer health research centers;

9/ set and supervise the enforcement of health service standards;

10/ determine the qualification requirement of professionals desiring to engage in public health service at various levels, and issue certificates of competence to them;

11/ ensure the carrying out of drug administration and control activities;

12/ delegate part of its powers to regional health bureaus and other government organs as deemed necessary.

## 23. The Ministry of Justice

The Ministry of Justice shall have the powers and duties to:

1/ be chief advisor to the Federal Government on matters of law;

2/ represent the Federal Government in criminal suits falling under the jurisdiction of the federal courts;

3/ order the conduct of investigation where it believes that a crime the adjudication of which falls under the jurisdiction of the federal courts has been committed; order the discontinuance of an investigation or instruct for further investigation on good cause; withdraw criminal charges in accordance with the law;

፬/ የወንጀል መነሻዎችንና የመከላከያ ዘዴዎችን ያጠናል፣ ወንጀል የሚቀንስበትን ሥልት ይቀይሳል፤ በወንጀል መከላከል ረገድ የሚመለከታቸውን መንግሥታዊ አካላት ያስተባብራል፤

፭/ የወንጀል ድርጊት ምስክሮች እንዳስፈላጊነቱ ጥበቃ እንዲያገኙ ያደርጋል፤

፮/ በወንጀል ድርጊት ወይም በሰብአዊ መብት መጣስ ምክንያት ከባድ ጉዳት ደርሶባቸው በፌዴራል ፍርድ ቤቶች ክስ ለመመስረትና ለመከራከር አቅም የሌላቸው ግለሰቦች ካሣ እንዲያገኙ በፍትሐብሔር ክስ ይረዳል፤

፯/ የሕዝቡን እንዲሁም የፌዴራል መንግሥትን መብትና ጥቅም ለማስከበር አስፈላጊ ሆኖ ሲያገኘው በፌዴራልና በክልል ፍርድ ቤቶች፣ በማንኛውም ዳኝነት ሰሚ አካል ወይም የሽምግልና ጉባዔ ክስ ይመሰርታል፣ ክስ እንዲመሠረት ያደርጋል ወይም በማናቸውም ደረጃ ጣልቃ በመግባት ይከራከራል፤

፰/ የሃይማኖት ድርጅቶችን፣ ዓላማቸው ትርፍ ለማግኘት ያልሆኑ የውጭ ድርጅቶችን እንዲሁም ሥልጣኑ በሕግ ለሌላ የመንግሥት አካል ካልተሰጠ በስተቀር እንቅስቃሴያቸው በአዲስ አበባና በድሬደዋ ከተሞች የተወሰነ ወይም በአንድ ክልል ያልተወሰነ መንግሥታዊ ያልሆኑ ድርጅቶችንና ማኅበሮችን ይመዘግባል፤

፱/ የፌዴራል መንግሥት መሥሪያ ቤቶች ተከራካሪ የሚሆኑባቸውን የፍትሐብሔር ክሶችና የመብት ጥያቄዎች አያያዝ እንደአስፈላጊነቱ ይከታተላል፣ አስፈላጊ ሆኖ ሲያገኘው ሪፖርት እንዲቀርብለት ያደርጋል፣ ለዚሁም ብቃት ያለው የሰው ኃይል መመደቡን ያረጋግጣል፤

፲/ በፌዴራል መንግሥት አካላትና በክልሎች ጥያቄ ሲቀርብለት የሕግ ረቂቆች በማዘጋጀት ይረዳል፤

፲፩/ በፌዴራል ፍርድ ቤቶች መከራከር ለሚችሉ ጠበቆች ፈቃድ ይሰጣል፣ ይቆጣጠራል፣ ይሠርዛል፤

፲፪/ ከሰብአዊ መብት አጠባበቅ አንፃር የሕዝብን ንቃተ ሕግ ለማዳበር በተለያዩ ዘዴዎች የሕግ ትምህርት ይሰጣል፤ የሕግ ትምህርትንና ሥልጠናን በሚመለከት ከሚመለከታቸው አካላት ጋር ይተባበራል፤

4/ study the causes crimes and the methods for prevention them; devise ways and means crime prevention; coordinate the relevant government organs in crime prevention;

5/ ensure that witnesses to criminal cases are accorded protection, as necessary;

6/ assist victims of crimes or violations of human rights in civil proceedings to claim damages where such victims are unable to institute such claims in the federal courts and to follow up the proceedings on their own;

7/ Institute or cause the institution of suits or intervene at any stage of the proceedings of such suits before federal and regional state courts, any judicial body or arbitration tribunal where the rights and interests of the public and of the Federal Government so require;

8/ register religious organizations, non-profit making foreign organizations and, unless specific power is given to other government organs, non-governmental organizations and associations operating in the cities of Addis Ababa and Dire Dawa or in more than one Regional State;

9/ follow up, as necessary, the handling of civil sots and claims to which the federal government organs are parties; cause reports to be submitted to it on same, and ensure that competent staff is assigned for the purpose;

10/ assist in the preparation of draft laws when so requested by federal and regional state organs;

11/ issue, supervise and revoke licenses to advocates for practicing before federal courts;

12/ provide legal education through the use of various methods with a view to raising public legal consciousness in relation to the protection of human rights; cooperate with the appropriate bodies regarding legal education and training;

፲፫/ የሕግ ማሻሻያ ጥናቶችን እንዲሁም የኮዲፊኬሽንና የፌዴራል ሕጎችን የማጠቃለል ሥራ ያካሂዳል፤ የክልሎችን ሕጎች ያሰባስባል፣ እንደአስፈላጊነቱም እንዲጠቃለሉ ያደርጋል፡፡

## ፳፬. የአገር መከላከያ ሚኒስቴር

የአገር መከላከያ ሚኒስቴር የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባሮች ይኖሩታል፤

፩/ አግባብ ካላቸው አካላት ጋር በመተባበር የአገሪቱን የግዛት ሉዐላዊነት ያስከብራል፤

፪/ መከላከያ ሠራዊት ያቋቁማል፣ ያስታጥቃል፣ ይቆጣጠራል፣ የውጊያ ብቃቱን ያረጋግጣል፤

፫/ የሀገሪቱ የመከላከያ ሠራዊት የብሔሮች፣ የብሔረሰቦችና የሕዝቦችን ሚዛናዊ ተዋጽኦ ያካተተ መሆኑንና ተግባሩንም ከፖለቲካ ድርጅት ወገናዊነት ነፃ በሆነ አኳኋን ማከናወኑን ያረጋግጣል፤

፬/ የመከላከያ ሠራዊት ማሠልጠኛ ተቋማት እንዲደራጁ ያደርጋል፤

፭/ ከክልል አቅም በላይ የሆነ የፀጥታ መደፍረስ ሲያጋጥም ወይም ማናቸውም ክልል ሕገ መንግሥቱን በመጣስ ሕገ መንግሥታዊ ሥርዓቱን አደጋ ላይ ሲጥል በሕገ መንግሥቱ በተደነገገው መሠረት ሲታዘዝ ፀጥታንና ሕገ መንግሥታዊ ሥርዓቱን ያስከብራል፤

፮/ የሽምቅ ውጊያንና ሽብርተኝነትን ይከላከላል፤

፯/ አገር መከላከልን በሚመለከት አግባብ ያላቸውን የፌዴራልና የክልል አካላት ያስተባብራል፣ በመተባበርም ይሠራል፤

፰/ የጦር ሠፈሮችንና ለሠራዊቱ የሚያስፈልጉትን የመኖሪያ ሠፈሮች ይሠራል፣ ያሠራል፤

፱/ በክተት ጊዜ በአገር ውስጥ የሚገኝ ሃብት በተቀናጀ ሁኔታ ጥቅም ላይ የሚውልበትን ዘዴ እያጠና ያስወስናል፤

፲/ የክተት አዋጅ በሚታወጅበት ጊዜ ኅብረተሰቡ ከጠላት ጥቃት ራሱን የሚከላከልበትን ዕቅድ ያወጣል፣ ሲፈቀድም ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመተባበር ሥራ ላይ እንዲውል ያደርጋል፤

13/ undertake legal reform studies and carry out the codification and consolidation of federal laws; collect regional State laws and consolidate same as necessary.

## 24. The Ministry of National Defense

The Ministry of National Defense shall have the powers and duties to:

1/ in cooperation with the appropriate organs, defend the territorial integrity of the country;

2/ establish, equip and supervise the defense forces and ensure their combat capabilities;

3/ ensure that the composition of the national defense forces reflect equitable representation of nations, nationalities and peoples and that they carry out their functions free of any partisanship to any political organization;

4/ organize training establishments for the defense forces;

5/ enforce security measures and the constitutional order, when instructed in accordance with the provisions of the Constitution, where situations endangering public safety are beyond the control of Regional States or where by Regional State violates the Constitution and endangers the constitutional order;

6/ combat guerrilla and terrorist activities;

7/ coordinate the activities of, and cooperate with the appropriate federal and regional state organs in matters relating to the defense of the country;

8/ construct and cause the construction of military comps and residential quarters required for the defense forces;

9/ prepare plans and get authorizations for the coordinated utilization of resources in the country that may be required in an event of national mobilization

10/ prepare schemes whereby the public can defend itself or guard against enemy threats when general mobilization is declared; and, upon authorization, implement same in cooperation with concerned organs;

፲፩/ በጦርነት ወይም በአስቸኳይ ጊዜ አዋጅ የመከላከያ ሠራዊትን የሚቀላቀል፣ እንዲሁም ሰው ሠራሽም ሆነ የተፈጥሮ አደጋዎች ሲከሰቱ ዕገዛ የሚያደርግ ብሔራዊ ተጠባባቂ ኃይል ይመለምላል፣ ያሰለጥናል፣ ያደራጃል፤

11/ recruit, train and organize national reserve force that shall join the Armed Forces in time of war or state of emergency and that provide assistance in the event of man-made or natural disasters;

፲፪/ የመከላከያ ኢንዱስትሪ ውጤቶችን የሚያመርቱ፣ የሚያድሱና የሚጠግኑ ድርጅቶች ያቋቁማል፣ ያስተዳድራል፤

12/ establish and administer enterprises that may engage in the production, maintenance and repair of defense industry products;

፲፫/ የመከላከያ ተቋማት በሰላም ጊዜ የሚኖራቸውን የማምረትና አገልግሎት የመስጠት ትርፍ አቅም ለገቢ ማስገኛ ተግባር እንዲውል በማድረግና ለመከላከያ ጠቀሜታ የሚያስፈለጉ ንብረቶችን በማስወገድ የሚገኘውን ገቢ እንዲሁም በተቆጣጣሪ ባለሥልጣንነት ከሚመራቸው የመከላከያ ኢንዱስትሪ ድርጅቶች የሚገኘውን የትርፍ ድርሻ የሚኒስትሮች ምክር ቤትን እያስፈቀደ ለሀገር መከላከያ አቅም ግንባታ እንዲውል ያደርጋል፤

13/ retain revenue generated by engaging idle production and service rendering capacities of defense institutions, in peace times, in income generating activities and the proceeds obtained from the disposal of properties which are no more required for defense purposes as well as dividends from defense industries put under its supervision, and utilize such fund upon obtaining the approval of the Council of Ministers, for national defense capacity building projects;

፲፬/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ /፲፫/ የተመለከተው ገንዘብ አስተዳደር በፋይናንስ አስተዳደር አዋጅ ቁጥር ፶፯/፲፱፻፹፱ እና በአዋጁ መሠረት በወጡ ደንቦችና መመሪያዎች የተደነገጉትን ሥርዓቶችና መመዘኛዎች ተከትሎ መፈጸሙን ያረጋግጣል፣ በዋናው ኦዲተርም እንዲመረመር ያደርጋል፤

14/ ensure that the procedures and standards embodied in the Financial administration Proclamation No. 57/1996 and regulations and directives issued there under are followed in the administration of the fund referred o in Sub-Article (13) of this Article and submit same for auditing by the Auditor General;

፲፭/ የሠራዊቱ አባላት በሠላም ጊዜ በአገሪቱ የልማት ሥራዎች እንዲሳተፉ ያደርጋል፤

15/ ensure that the defense forces participate in the country's development activities in times of peace;

፲፮/ አገሪቱ የሚቀርብላትን አለም አቀፍ የሰላም ማስከበር ጥሪ በአግባቡ ለመወጣት የሚያስችል የሰላም አስከባሪ ኃይል ያደራጃል፣ ያሰማራል።

16/ organize and deploy competent peacekeeping forces where the country is required to participate in international peacekeeping missions.

## ፳፭. የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር

## 25. The Ministry of Foreign Affairs

የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባሮች ይኖሩታል፤

The Ministry of Foreign Affairs shall have the powers and duties to:

፩/ አገሪቱ በሚኖራት የውጭ ግንኙነት ጥቅሟና መብቷ እንዲጠበቅና በሌሎች መንግሥታት እንዲከበር ያደርጋል፤

1/ safeguard the interests and rights of the country in connection with its foreign relations and ensure that they are respected by foreign states;

፪/ አገሪቱ ከጎረቤት አገሮች ጋር ያላት መልካም ጉርብትና እንዲጠናከር ያደርጋል፤

2/ ensure that the country's good relations with neighboring countries are strengthened;

፫/ የኢኮኖሚ ዲፕሎማሲ በማካሄድ፣

ሀ) የአገሪቱን የውጭ ንግድና ቱሪዝም በማስፋፋት፣
ለ) የውጭ ኢንቨስተሮችን በመለየትና በመሳብ፣
ሐ) የውጭ የልማት ፋይናንስና የቴክኒክ ተራድኦ የሚገኝበትን ሁኔታ በማመቻቸት፣

ረገድ ከሚመለከታቸው አካላት ጋር ይተባበራል፤

፬/ በውጭ አገር የሚኖሩ ኢትዮጵያዊያን መብትና ጥቅም እንዲጠበቅ ያደርጋል፤ በኢትዮጵያዊያን ማኅበረሰብና በኢትዮጵያ ዊያን ወዳጆች የተመሠረቱ ማኅበራትን ያበረታታል፣ ድጋፍ ይሰጣል፤

፭/ ሥልጣኑ በተለይ ለሌላ አካል በሕግ ካልተሰጠ በስተቀር፣ ኢትዮጵያ ከሌሎች መንግሥታትና ዓለም ዓቀፍ ድርጅቶች ጋር የምታደርጋቸውን በመንግሥት የተፈቀደ ዓለም አቀፍ ውሎች ጉዳዩ ከሚመለከ ታቸው አካላት ጋር በመመካከር ይፈርማል፤ እንዲሁም ዓለም አቀፍ ውሎች እንዲጸድቁ ለማድረግ የሚያስፈልጉትን ፎርማሊቲዎች ሁሉ ያከናውናል፤

፮/ ሌሎች የመንግሥት አካላት ከውጭ አገር መንግሥታትና ከዓለም ዓቀፍ ድርጅቶች ጋር የሚያደርጓቸውን ግንኙነቶች ያስተባብራል፤

፯/ በኢትዮጵያ ከሚገኙ የውጭ አገሮች መንግሥታት እንደራሴዎች፣ ቆንስሎችና የዓለም ዓቀፍ ድርጅቶች ወኪሎች ጋር እንደ አስፈላጊነቱ በመገናኘት የጋራ ጥቅሞች የሚጠበቁበትን ሁኔታ ያመቻቻል፤

፰/ በውጭ አገር የኢትዮጵያ የዲፕሎማቲክና የቆንስላ ሚስዮኖችን እንዲሁም በዓለም ዓቀፍ ድርጅቶች የኢትዮጵያ ቋሚ መልእክተኞች ጽሕፈት ቤቶችን ተግባራት ያስተባብራል፣ ሥራቸውንም ይቆጣጠራል፤

፱/ ሥልጣኑ በተለይ ለሌላ አካል ካልተሰጠ በስተቀር፣ የኢትዮጵያ መንግሥት የፈረማ ቸው ዓለም ዓቀፍ ውሎች የሚያስከትሏቸው መብቶችና ግዴታዎች መከበራቸውን ያረጋግጣል፤

፲/ ኢትዮጵያ ከሌሎች መንግሥታትና ዓለም ዓቀፍ ድርጅቶች ጋር የምታደርጋቸውን ዓለም ዓቀፍ ውሎች የተመሰከረባቸውን ዋናዎቹን ቅጅዎች መዝግቦ ይጠብቃል፤

3/ through pursuing economic diplomacy, cooperate with the concerned organs in:

a) promoting the country's foreign trade and tourism;
b) identifying and attracting foreign investors;
c) facilitating the mobilization of external financial and technical assistances;

4/ ensure that the interests and the rights of Ethiopians residing abroad are protected; encourage and support associations formed by Ethiopian communities and friends of Ethiopia;

5/ in consultation with the concerned organs, negotiate and sign treaties that Ethiopia enters into with other states and international organizations and which are approved by the Government, except in so far as such power is specifically given by law to other organs; and effect all formalities of ratification of treaties;

6/ coordinate all relations of other government organs with foreign states and international organizations;

7/ keep contacts, as may be necessary, with foreign diplomatic and consular representatives in Ethiopia as well as with representatives of international organizations with a view to facilitating the protection of mutual interests;

8/ coordinate and supervise the activities of Ethiopia's diplomatic and consular missions and permanent missions of Ethiopia to international organizations;

9/ ensure the enforcement of rights and obligations arising from treaties signed by the Ethiopian Government except in so far as specific power has legally been delegated to other organs;

10/ register and keep all authentic copies of treaties concluded between Ethiopia and other states and international organizations;

፲፩/ የኢትዮጵያ መንግሥት በብዙ መንግሥታት መካከል የሚደረጉ ዓለም አቀፍ ውሎችን አስቀማጭ በሚሆንበት ጊዜ ይኸው ባለአደራነት የሚጠይቀውን ተግባር ያከናውናል፤

፲፪/ በዓለምአቀፍ ሕግና ኢትዮጵያ በተቀበለ ቻቸው ዓለምአቀፍ ውሎች ለውጭ አገር መንግሥታት እንደራሴዎችና ለዓለምአቀፍ ድርጅቶች ወኪሎች የተሰጡ መብቶች እንዲከበሩ ያደርጋል፤

፲፫/ አግባብ ባለው ሕግ መሠረት ዲፕሎማቲክና ሰርቪስ ፓስፖርቶች እና የዲፕሎማቲክና ሰርቪስ መግቢያ ቪዛዎች ይሰጣል።

## ፳፮. የማስታወቂያ ሚኒስቴር

የማስታወቂያ ሚኒስቴር የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባሮች ይኖሩታል፤

፩/ የመንግሥት ፖሊሲዎችን ያስተዋውቃል፣ ወቅታዊ የመንግሥት ኢንፎርሜሽን ያሰራጫል፤ ለዚህም የሚያስፈልገውን ሥርዓት ይዘረጋል፣ ይመራል፤

፪/ ብሔራዊ መግባባትን ለመፍጠር የሚያስችሉ እንዲሁም የአገሪቱን መልካም ገጽታ የሚያጎለብቱ የሚዲያ ፕሮግራሞች እንዲዘጋጁና እንዲሰራጩ ያደርጋል፤

፫/ የብሮድካስት አገልግሎት ለአገር ዕድገት አስተዋጽኦ ሊያበረክት በሚችል መልኩ መካሄዱን ያረጋግጣል፤

፬/ ለንግድ የሚቋቋሙ ፕሬሶችን ይመዘግባል፤ የንግድ ዓላማ ለሌላቸው ፕሬሶች እና ለጊዜያዊ ሥራ ለሚመጡም ሆነ ተቀማጭነታቸው ኢትዮጵያ ውስጥ ለሆኑ የውጭ አገር ዜና ወኪሎች ፈቃድ ይሰጣል፤

፭/ የማስታወቂያ ሥራ ሕግን ተከትሎ መከናወኑን ያረጋግጣል።

## ፳፯. የውሃ ሃብት ሚኒስቴር

የውሃ ሃብት ሚኒስቴር የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባሮች ይኖሩታል፤

፩/ የተፋሰስ ጥናት በማካሄድ የአገሪቱን የከርሰ ምድርና ገጸ ምድር የውሃ ሀብት አለኝታ በመጠንና በጥራት ይለያል፣ ጥቅም ላይ የሚውልበትን ሁኔታ ያመቻቻል፤

11/ perform the functions of a depository of multilateral treaties when the Ethiopian Government is a depository of such treaties;

12/ ensure that privileges and immunities accorded to foreign diplomatic missions and representatives of international organizations under international laws and treaties to which Ethiopia is a party are respected;

13/ issue diplomatic and service passports and diplomatic and service entry visas in accordance with the relevant laws.

## 26. The Ministry of Information

The Ministry of Information shall have the powers and duties to:

1/ popularize government policies and disseminate current government information; establish and direct a system required for same;

2/ cause the production and transmission of media programs that could promote national consensus and the country's image building;

3/ ensure that broadcast services are conducted in a manner that contributes to the development of the country;

4/ register commercial press; issue permit to non-profit making press and foreign news correspondents stationed in Ethiopia either temporarily or permanently;

5/ ensure that advertisements are conducted in compliance with legal requirements.

## 27. The Ministry of Water Resources

The Ministry of Water Resources shall have the powers and duties to;

1/ undertake basin studies and determine the country's ground and surface water resource potential in terms of volume and quality, and facilitate the utilization of same;

፪/ ከአንድ በላይ የሆኑ ክልሎችን አቋርጦ የሚፈስ ወይም የሚያዋስን ውሃ በልዩ ልዩ የግልጋሎት ዓይነቶችና በክልሎች መካከል ሚዛናዊ በሆነ መንገድ የሚከፋፈልበትንና ጥቅም ላይ የሚውልበትን ሁኔታ ይወስናል፤

፫/ በወሰንና ወሰን ተሻጋሪ የውሃ አካላት አጠቃቀም ላይ ጥናት ያካሂዳል፣ አለም አቀፍ ውሎችን ይደራደራል፣ አፈጻጸማቸውን ይከታተላል፤

፬/ የመካከለኛና የከፍተኛ መስኖ ልማት ሥራዎችን ለማስፋፋት የሚያስችሉ የጥናት፣ የዲዛይንና የግንባታ ሥራዎች እንዲካሄዱ ያደርጋል፤

፭/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ /፪/ እና /፫/ በተጠቀሱት የውሃ አካሎች ላይ የውሃ ሥራዎች ለመሥራትና በጥቅም ላይ ለማዋል ፈቃድ ይሰጣል፣ ይቆጣጠራል፤

፮/ ለሚመለከታቸው ሌሎች አካላት እንዲተላለፉ ካልተደረገ በስተቀር፣ በፌዴራል መንግሥት በጀት የተገነቡ ግድቦችንና የውሃ ውቅሮችን ያስተዳድራል፣

፯/ የሚቲዎሮሎጂ አገልግሎት ሥራ እንዲከናወን መደረጉን ያረጋግጣል።

፳፰. የወጣቶችና ስፖርት ሚኒስቴር

የወጣቶችና ስፖርት ሚኒስቴር የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባሮች ይኖሩታል፤

፩/ ወጣቶች በነፃ ፍላጎታቸው ተደራጅተው በሀገሪቱ የዲሞክራሲ ሥርዓት ግንባታ፣ መልካም አስተዳደርና ልማት እንቅስቃሴ እንዲሳተፉ ተገቢውን ድጋፍ ያደርጋል፤

፪/ የወጣቶች ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ችግሮች እንዲፈቱ ምቹ ሁኔታዎችን ይፈጥራል፤

፫/ የተደራጁ ወጣቶች ተገቢውን የቴክኒክ፣ የማቴሪያልና የፋይናንስ ድጋፎች እንዲያገኙ ያደርጋል፤

፬/ በየጊዜው የወጣቶችን ሁኔታ የሚያመለክቱ ዝርዝር መረጃዎች ይሰበስባል፤

፭/ ወጣቶችን በሚመለከቱ ጉዳዮች የተለያዩ አካላት የሚያደርጓቸውን እንቅስቃሴዎች ያስተባብራል፤

2/ determine conditions and methods required for the optimum and equitable allocation and utilization of water bodies that flow across or lie between more than one Regional States among various uses and the regional States;

3/ undertake studies and negotiations of treaties pertaining to the utilization of boundary and trans-boundary water bodies, and follow up the implementation of same;

4/ cause the carrying out of study, design and construction works to promote the expansion of medium and large irrigation dams;

5/ issue permits and regulate the construction and operation of water works relating to water bodies referred to in Sub-Article (2) and (3) of this Article;

6/ administer dams and hydraulic structures constructed by federal budget unless they are entrusted to the authority of other relevant bodies;

7/ ensure the provision of meteorological services.

**28. The Ministry of Youth and Sports**

The Ministry of Youth and Sports shall have the powers and duties to:

1/ provide the necessary support to enable the youth to form voluntary organizations and participate in the promotion of the country's democratic process, good governance and development;

2/ create conducive conditions to mitigate the economic and social problems facing the youth;

3/ ensure that appropriate technical, material and financial supports are provided to the organized youth;

4/ collect detailed periodical information pertaining to the youth;

5/ coordinate the activities of various bodies on issues involving the youth;

፮/ ሕዝቡን በስፖርት ለሁሉምና ባሕላዊ ስፖርት ተሣታፊና ተጠቃሚ ያደርጋል፤

፯/ የሠለጠነ የሰው ኃይል ማፍራትና ብቃትን ለማሳደግ የስፖርት ትምህርት፣ ሥልጠናና ምርምር ተቋሞች የሚቋቋሙበትን ሥልት በመቀየስ ተግባራዊ እንዲሆን ያደርጋል፤

፰/ የስፖርት ማዘውተሪያ ሥፍራዎችንና የስፖርት ማበልፀጊያ ማዕከላትን ያስፋፋል፤

፱/ ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመተባበር የስፖርት ህክምና አገልግሎት ያደራጃል፤ በስፖርት አበረታች መድኃኒቶችና ዕፆች መጠቀመን ለመከላከል የሚያስችል ሥርዓት ይዘረጋል፤

፲/ የስፖርት ማኅበራት ስለሚቋቋሙበት ሁኔታ መመሪያ ያወጣል፤ በፌዴራል ደረጃ የሚቋቋሙ የስፖርት ማኅበራትን ይመዘግባል፣ አስፈላጊውን ድጋፍ ይሰጣል።

## ፳፱. የሴቶች ጉዳይ ሚኒስቴር

የሴቶች ጉዳይ ሚኒስቴር የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባሮች ይኖሩታል፤

፩/ በአገር አቀፍ ደረጃ ሴቶችን መብትና ጥቅም ለማስከበር የሚረዱ ሃሣቦችን ያመነጫል፤ ስልት በመቀየስ ለተግባራዊነቱ አስፈላጊውን ክትትል ያደርጋል፤

፪/ በፌዴራል መንግሥት አካላት የሚዘጋጁ ፖሊሲዎች፣ ሕጎች፣ የልማት ፕሮግራሞችና ፕሮጀክቶች የሥርዓተ ፆታን ጉዳይ እንዲያካትቱ ስልት በመንደፍ አስፈላጊውን ክትትል ያደርጋል፤

፫/ ሴቶች በሀገሪቱ የፖለቲካ፣ የኢኮኖሚና የማኀበራዊ እንቅስቃሴዎች ውስጥ በንቃት ለመሳተፍ የሚያስችሏቸው ዕድሎች የተመቻቹላቸው መሆኑን ያረጋግጣል፣

፬/ በሴቶች ላይ የሚቃጡ መድሎዎችን በጥናት በመለየት መድሎዎቹ የሚወገዱባቸውን የመፍትሔ ሃሣቦች ያቀርባል፤ አፈጻጸሙን ይከታተላል፤

፭/ ሴቶች ለዘመናት በበታችነትና በልዩነት በመታየታቸው የደረሰባቸውን ጭቆና ከግምት ውስጥ በማስገባት በኢኮኖሚ፣ በማህበራዊና በፖለቲካ ጉዳዮች ተሳትፎአቸውን ለማሳደግ ልዩ ትኩረትና ድጋፍ መስጠት ስለሚቻልበት ሁኔታ ሃሳብ ያቀርባል፤ ተግባራዊነቱንም ይከታተላል፤

6/ enable the public to participate in and benefit from sports-for-all and cultural sports;

7/ formulate and implement strategies for the establishment of sports education, training and research institutions necessary for the development of trained human resource and promotion of competence;

8/ promote the expansion of sport facilities and centers;

9/ in cooperation with the appropriate bodies, organize sports medical facilities, and adopt systems for controlling doping practices;

10/ issue directives on the establishment of sport associations register sports associations operating at the national level and provide them with the necessary support.

## 29. The Ministry of Women's Affairs

The Ministry of Women's Affairs shall have the powers and duties to:

1/ initiate recommendations on the protection of the rights and interests of women at national level, and follow up the implementation of same by devising strategies;

2/ follow up, by designing strategies, that the preparation of policies, legislations, development programs and projects by federal government organs give due consideration to gender issues;

3/ ensure that opportunities are created for women to actively participate in political, economic and social activities;

4/ undertake studies to identify discriminatory practices affecting women; submit recommendations on elimination of such practices and follow up their implementation;

5/ submit recommendations on the application of affirmative measures in order to promote the participation of women in economic social and political affairs by taking into account the oppression they faced for centuries as a result of inequality and discrimination;

፮/ ሴቶች በተለያዩ የመንግሥት አካላት በውሣኔ ሰጪ የሥራ ቦታዎች ለመመደብ በቂ ትኩረት የተሰጣቸው መሆኑን ያረጋግጣል፤

፯/ ሴቶች እንደፍላጎቶቻቸውና እንደችግሮቻቸው ተደራጅተው ለመብቶቻቸው እንዲታገሉና ችግሮቻቸውን ማስወገድ እንዲችሉ ያበረታታል፣ ሁኔታዎችን ያመቻቻል፤

፰/ ሴቶችንና ሕጻናትን የሚመለከቱ ዓለም አቀፍ ውሎችን አፈጻጸም ይከታተላል፤ ለሚመለከታቸው አካላትም ወቅታዊ ሪፖርት ያቀርባል፤

፱/ የሀገሪቱ የሴቶች ፖሊሲ ተግባራዊ እንዲሆን በአገር አቀፍ ደረጃ ይከታተላል፣ ያስተባብራል፤

፲/ በዝቅተኛ የኑሮ ደረጃ ላይ የሚገኙ ሴቶችን የኑሮ ሁኔታ ለማሻሻል የሚረዱ ጥናቶችን ያስጠናል፣ ፕሮግራሞችንና ፕሮጀክቶችን በመቅረጽ ተግባራዊ ያደርጋል፤ ለዚሁ ዓላማ ለሚንቀሳቀሱ ድርጅቶችም አስፈላጊውን እገዛ ያደርጋል፤

፲፩/ የእናቶችና የሕፃናት ደኅንነት ስለሚሻሻልበት ሁኔታ ያጠናል፣ ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመተባበርም ተግባራዊ እንዲሆን ያደርጋል፤

፲፪/ መንግሥታዊ ካልሆኑ ድርጅቶች፣ ከተለያዩ የማህበረሰብ ተቋማትና ከሴቶች ማኅበራት ጋር ሴቶችን በሚመለከቱ ጉዳዮች ዙሪያ አብሮ ይሠራል፣ ሁኔታዎችን ያመቻቻል፡፡

## ፴. የባህልና ቱሪዝም ሚኒስቴር

፩/ የባህልና ቱሪዝም ሚኒስቴር የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባሮች ይኖሩታል፤

ሀ) የኢትዮጵያ ብሔር፣ ብሔረሰቦችና ሕዝቦች ታሪክ፣ ባህላዊ ቅርሶችና እሴቶች እንዲጠኑና እንዲጠበቁ ያደርጋል፤

ለ) በባህል ተፅእኖ ሳቢያ ማህበራዊ እድገትን የሚያጓትቱ አመለካከቶችን፣ እምነቶችንና ልማዳዊ አሰራሮችን የመለወጥ ተግባሮች ያከናውናል፤

ሐ) የባህል ዘርፉ ልማታዊ አስተዋጽኦ እንዲስፋፋ ያደርጋል፤

መ) በባህል ዘርፍ የሕዝቡን ተሳትፎ ተቋማዊ መሠረት ለማስያዝ የባህል ተቋማት እንዲስፋፉ ያደርጋል፤

6/ ensure that the necessary attention is given to place women to decision-making positions in various government organs;

7/ encourage and facilitate women to be organized, based on their free will and needs, with a view to defending their rights and solving their problems;

8/ follow up the implementation of treaties concerning women and children and submit periodical reports to the concerned organs;

9/ follow up and coordinate, at national level, the implementation of the country's policy on women's affairs;

10/ sponsor studies and formulate and implement programs and projects contributing to the improvement of the living conditions of needy women, and give the necessary support to organizations operating for achieving the said objective;

11/ undertake studies to promote the well-being of mothers and children and implement same in cooperation with other organs;

12/ collaborate with non-governmental organizations, civic organizations and women's associations on issues concerning women, and create conducive environment for their activities.

## 30. The Ministry of Culture and Tourism

1/ The Ministry of Culture and Tourism shall have the powers and duties to:

a) cause the study and preservation of history, cultural heritages and values of the nations, nationalities and peoples of Ethiopia;

b) induce changes in cultural attitudes, beliefs and practices retarding social progress;

c) promote the contribution of culture to development;

d) expand cultural institutions to institutionalize public participation in the field of culture;

ሠ) የአገሪቱን የቱሪዝም መስሕቦችና መልካም ገጽታ በዓለም የቱሪዝም ገበያ በሥፋት ያስተዋውቃል፤ የአገር ውስጥ ቱሪዝም እንዲስፋፋ ያበረታታል፤

ረ) የአገሪቱ ቱሪስት መስሕቦች ተለይተው እንዲታወቁና ለቱሪዝም አመቺ ሆነው እንዲለሙና እንዲደራጁ፣ የቱሪስት አገልግሎት ሰጪ ድርጅቶች እንዲስፋፉ፣ የየአካባቢው ማኅበረሰብም ከቱሪዝም ጥቅሞች ተካፋይ እንዲሆን ያደርጋል፤

ሰ) የቱሪስት አገልግሎት ሰጪ ተቋማትን ደረጃዎች ይወስናል፣ ተፈጻሚነቱን ይቆጣጠራል፤

ሸ) በቱሪዝም የሠመረ አገልግሎት እንዲኖርና የቱሪስቶችም ደህንነት እንዲረጋገጥ የሚያስፈልገው የብዙ ወገኖች የሥራ ቅንጅት እውን እንዲሆን ለሚፈጠሩ የጋራ መድረኮች በማዕከልነት ያገለግላል፤

ቀ) በሰው ኃይል ሥልጠናና በሙያ ምክር አገልግሎት አማካይነት የቱሪዝም ሴክተርን የማስፈጸም አቅም ይገነባል፤

በ) የባህልና ቱሪዝም መረጃዎችን ያሰባስባል፣ ያጠናቅራል፣ ያሰራጫል፡፡

፪/ በሥራ ላይ ባሉ የሌሎች ሕጎች ድንጋጌዎች ለቱሪዝም ኮሚሽን እንዲሁም የባህል ዘርፍን በሚመለከት ለወጣቶች፣ ባህልና ስፖርት ሚኒስቴር ተሰጥተው የነበሩ ሥልጣንና ተግባሮች በዚህ አዋጅ ለባህልና ቱሪዝም ሚኒስቴር ተሰጥዋል፡፡

## ፴፩. <u>የማዕድንና ኢነርጂ ሚኒስቴር</u>

የማዕድንና ኢነርጂ ሚኒስቴር የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባሮች ይኖሩታል፤

፩/ የማዕድንና ኢነርጂ ልማት እንዲስፋፋ ያደርጋል፤

፪/ የማዕድንና ኢነርጂ መረጃዎች በአግባቡ እንዲሰበሰቡ፣ እንዲጠበቁና ለተጠቃሚዎች እንዲቀርቡ ያደርጋል፤

፫/ የማዕድን ፍለጋና ልማት ምቹ ሁኔታ በመፍጠር የማዕድን ኢንቨስትመንትን ያበረታታል፤

e) promote widely the country's tourist attractions and its positive image on the world tourism market, and encourage domestic tourism;

f) ensure that the country's tourist attractions are identified, properly developed and organized, tourist facilities are expanded, and that local communities share the benefits derived from tourism;

g) set and supervise the enforcement of standards for tourist facilities;

h) serve as a focal point for forums established to facilitate the coordination of the multi-sectoral efforts required for the provision of quality tourist services and for ensuring the well-being of tourists;

i) build the capacity of the tourism sector through the provision of human resource training and consultancy services;

j) collect, compile and disseminate information on culture and tourism.

2/ The powers and duties given to the Tourism Commission and, with respect to cultural sector, to the Ministry of Youth, Sports and Culture by the provisions of other laws, currently in force, are hereby given to the Ministry of Culture and Tourism.

## 31. The Ministry of Mines and Energy

The Ministry of Mines and Energy shall have the powers and duties to:

1/ promote the development of mining and energy;

2/ ensure the proper collection and maintenance of depository of mineral and energy data and their accessibility to users;

3/ encourage mining investment through facilitating exploration and mining operations;

፬/ በማዕድን ፍለጋና ልማት ለሚሠማሩ የግል ባለሃብቶች ፈቃድ ይሰጣል፤ በገቡት ውል መሠረትም ሥራቸውን ማካሄዳቸውንና የክፍያ ግዴታዎቻቸውን መፈጸማቸውን ይቆጣጠራ፤

፭/ ስለኢነርጂ ልማትና አጠቃቀም ጥናት ያካሂዳል፤ የሀገሪቱ ኤሌክትሪክ ኃይል አቅርቦት እንዲያድግና እንዲስፋፋ ያደርጋል፤

፮/ የነዳጅ ምርቶች ማከማቻና ማከፋፈያ ተቋሞችን ደረጃ ይወስናል፣ ተፈጻሚነቱን ይከታተላል፤

፯/ አግባብ ካላቸው አካላት ጋር በመተባበር የነዳጅ መጠባበቂያ ክምችትን መጠን ይወስናል፣ ክምችቱ እንዲኖር መደረጉን ያረጋግጣል፣

፰/ ከሚመለከታቸው ጋር በመተባበር በባህላዊና በአነስተኛ ደረጃ የሚመረቱ የከበሩና ጌጣጌጥ ማዕድናት ግብይት ህጋዊ መስመር እንዲይዝ ያደርጋል፤

፱/ የማዕድን ልማትን ለማፋጠን የሚረዱ የምርምርና የማሠልጠኛ ተቋሞች እንዳስፈላጊነቱ ያቋቁማል።

## ፴፪. <u>የሠራተኛና ማህበራዊ ጉዳይ ሚኒስቴር</u>

የሠራተኛና ማህበራዊ ጉዳይ ሚኒስቴር የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባሮች ይኖሩታል፤

፩/ የኢንዱስትሪ ሰላም እንዲጠበቅ፣

ሀ) ሠራተኞችና አሠሪዎች በማህበር የመደራጀትና የሕብረት ድርድር የማድረግ መብቶቻቸውን እንዲጠቀሙ ያበረታታል፣ ድጋፍ ይሰጣል፤

ለ) በአሠሪዎችና በሰራተኞች መካከል የሁለትዮሽ እንዲሁም የመንግሥት ወገንን ጨምሮ የሦስትዮሽ አሠራሮች እንዲለመዱ ያደርጋል፤

ሐ) የሥራ ክርክሮች በተቀላጠፈ መንገድ መፍትሄ እንዲያገኙ የሚያስችሉ አሠራሮችን ይዘረጋል፤

፪/ የሙያ ጤንነትና ደህንነት አጠባበቅ ደረጃዎችን ያወጣል፣ ሥራ ላይ መዋሉንም ይከታተላል፤

4/ issue licenses to private investors engaged in exploration and mining operations, and ensure that they conduct mining operations and meet financial obligations in accordance with their concession agreements;

5/ undertake studies concerning the development and utilization of energy; and promote the growth and expansion of the country's supply of electric energy;

6/ set standards for petroleum storage and distribution facilities, and follow up the enforcement of same;

7/ in cooperation with the appropriate organs, determine the volume of petroleum reserve and ensure that it is maintained;

8/ regulate, in cooperation with the concerned organs, the market for precious and ornamental minerals produced at the level of traditional and small-scale mining operations;

9/ establish, as may be necessary, research and training centers that may assist the enhancement of the development of mining and energy.

## 32. The Ministry of Labour and Social Affairs

The Ministry of Labour and Social Affairs shall have the powers and duties to:

1/ with a view to ensuring the maintenance of industrial peace:

a) encourage and support workers and employers to exercise their right to organize and collective bargaining;

b) encourage the practice of participating in bilateral forums between workers and employers and tri-partite forums including the government;

c) establish efficient labour dispute settlement mechanisms;

2/ issue and follow up the implementation of occupational health and safety standards;

፫/ ቀልጣፋና ፍትሐዊ የሥራ ሥምሪት አገልግሎት ሊኖር የሚችልበትን ሁኔታ ያመቻቻል፤ ለውጭ አገር ሰዎች የሥራ ፈቃድ የሚሰጥበትን ሁኔታ ይወስናል፣ ፈቃድ ይሰጣል፤ የኢትዮጵያዊያን የውጭ አገር የሥራ ሥምሪት አገልግሎትን ይቆጣጠራል፤

፬/ በአገሪቱ ውስጥ መደበኛ በሆነና መደበኛ ባልሆነ ሥራ ላይ ስለተሰማራውና በሥራ አጥነት ስለሚገኘው የሰው ኃይልና ስለሙያ አመዳደብ ጥናት ያደርጋል፤ የሥራ ገበያ መረጃዎችን ይሰበስባል፣ ያጠናቅራል፣ ያሠራጫል፤

፭/ በአገር አቀፍ ደረጃ የሚደራጁትን የሠራ ተኛና የአሠሪ ማህበራት ይመዘግባል፤

፮/ ለፌዴራል መንግሥት ተጠሪ በሆኑ ከተሞች ውስጥ የሚገኙ የፌዴራል መንግሥት የልማት ድርጅቶችን የሚመለከቱ የሠራተኛ ማኅበራትንና የኅብረት ስምምነቶችን ይመዘ ግባል፤ በነዚሁ ድርጅቶች ውስጥ የሥራ ሁኔታ ቁጥጥር አገልግሎት ተግባሮችን ያከናውናል፤

፯/ የዜጎች ማህበራዊ ደህንነት የሚጠበቁባቸ ውንና የሚሻሻሉባቸውን ዘዴዎች በተለይም፣

ሀ) የቤተሰብ ደህንነት ስለሚጠበቅበትና ጋብቻ ስለሚጠናከርበት፣
ለ) የአካል ጉዳተኞች እኩል ዕድል ተጠቃሚና ሙሉ ተሳታፊ ሊሆኑ ስለሚችሉበት፣
ሐ) አረጋዊያን እንክብካቤ ስለሚያገኙበትና ተሳትፎአቸው ሊጎለብት ስለሚችልበት፣

ሁኔታ ያጠናል፣ ሥራ ላይ የሚውልበትን ሁኔታ ያመቻቻል::

## ፴፫. ስለሌሎች የፌዴራል አስፈጻሚ አካላት

፩/ በሚከተሉት ንዑስ አንቀጾች የተደረጉት የስያሜና የተጠሪነት ማሻሻያዎች እንደተ ጠበቁ ሆነው፣ የፌዴራል መንግሥቱ ሌሎች አስፈጻሚ አካላት የተቋቋሙባቸው ሕጎች በተደነገገው መሠረት ሥራቸውን ይቀጥላሉ::

፪/ የፌዴራል መንግሥት አስፈጻሚ አካላትና ኃላፊዎቻቸውን በሚመለከት ከዚህ አዋጅ ጋር ተያይዞ በሚገኘው ሠንጠረዥ የተመለከተው የስያሜ ማሻሻያ ተደርጓል:: የስያሜ ማሻሻያው በአስፈጻሚ አካላቱ ተጠሪነት እንዲሁም መብቶችና ግዴታዎች ላይ የሚያስከትለው ለውጥ አይኖርም::

3/ create conducive conditions for the provision of efficient and equitable employment services; determine conditions for the issuance of work permit to foreigners and issue such permits; regulate the provision of foreign employment services to Ethiopians;

4/ undertake studies on manpower employed in the formal and informal sectors, unemployed manpower and the classification of jobs in the country; collect, compile and disseminate information on labour market;

5/ register workers' and employers' unions established at national level;

6/ register workers' unions and collective agreements relating to federal public enterprises situated in cities accountable to the Federal Government, and carry out labour inspection services in such enterprises;

7/ undertake and facilitate the implementation of studies on ensuring and improving the social well-being of citizens, in particular, on;

a) the protection of family and marriage;

b) the creation of equal opportunity for persons with disabilities;

c) the provision of care to the elderly and the encouragement of their participation.

## 33. Other Federal Executive Organs

1/ Without prejudice to the amendments made under the provisions of the following Sub-Articles, other federal executive organs shall continue to function in accordance with the legislations establishing them;

2/ There is hereby made amendments to the designations of federal executive organs and their heads as specified in the Schedule attached hereto. The amendments made in designations shall have no effect with regard to the accountability as well as the rights and obligations of the executive organs.

፫/ የሚከተሉት አስፈጻሚ አካላት ተጠሪነት ለጠቅላይ ሚኒስትሩ ይሆናል፤

ሀ) የኢትዮጵያ ሳይንስና ቴክኖሎጂ ኤጀንሲ፤

ለ) ብሔራዊ የመረጃና ደህንነት አገልግሎት፤

ሐ) የማኅበራዊ ዋስትና ኤጀንሲ፤
መ) የኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ፡፡

፬/ የሚከተሉት አስፈጻሚ አካላት ተጠሪነት ለአቅም ግንባታ ሚኒስቴር ይሆናል፤

ሀ) የፌዴራል ሲቪል ሰርቪስ ኤጀንሲ፤
ለ) የኢትዮጵያ ሲቪል ሰርቪስ ኮሌጅ፤
ሐ) የፍትህና የሕግ ሥርዓት ምርምር ኢንስቲትዩት፡፡

፭/ የኢትዮጵያ ኢንቨስትመንት ኤጀንሲ ተጠሪነት ለንግድና ኢንዱስትሪ ሚኒስቴር ይሆናል፡፡

፮/ የኅብረት ሥራ ኤጀንሲ ተጠሪነት ለግብርናና ገጠር ልማት ሚኒስቴር ይሆናል፡፡

፯/ የሚከተሉት አስፈጻሚ አካላት ተጠሪነት ለሥራና ከተማ ልማት ሚኒስቴር ይሆናል፤

ሀ) የኢትዮጵያ መንገዶች ባለሥልጣን፤
ለ) የመንገድ ፈንድ ጽሕፈት ቤት፤
ሐ) የፌዴራል የከተሞች ፕላን ኢንስቲትዩት፤
መ) የኪራይ ቤቶች ኤጀንሲ፡፡

፰/ የሚከተሉት አስፈጻሚ አካላት ተጠሪነት ለገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር ይሆናል፡፡

ሀ) የማዕከላዊ ስታትስቲክስ ኤጀንሲ፤
ለ) የኢትዮጵያ ካርታ ሥራ ኤጀንሲ፤
ሐ) የመንግሥት የልማት ድርጅቶች ባላደራ ቦርድ፡፡

፱/ የሚከተሉት አስፈጻሚ አካላት ተጠሪነት ለገቢዎች ሚኒስቴር ይሆናል፤

ሀ) የኢትዮጵያ ጉምሩክ ባለሥልጣን፤
ለ) የብሔራዊ ሎተሪ አስተዳደር፡፡

፲/ የኢትዮጵያ ፈንጂ አምካኝ ጽሕፈት ቤት ተጠሪነት ለፌዴራል ጉዳዮች ሚኒስቴር ይሆናል፤

3/ The following executive organs shall be accountable to the Prime Minister:

a) the Ethiopian science and Technology Agency;
b) the National Intelligence and Security Service;
c) the Social security Agency;
d) the National Bank of Ethiopia;

4/ The following executive organs shall be accountable to the Ministry of Capacity Building;

a) the Federal Civil Service Agency;
b) the Ethiopian Civil service College;
c) the Justice and Legal System Research Institute.

5/ The Ethiopian Investment Agency shall be accountable to the Ministry of Trade and Industry.

6/ The Cooperatives Agency shall be accountable to the Ministry of Agriculture and Rural Development;

7/ The following executive organs shall be accountable to the Ministry of Works and Urban Development:

a) the Ethiopian Roads Authority;
b) the Office of the Road Fund.
c) the Federal Urban Planning Institute;
d) the Rented Houses Agency.

8/ The following executive organs shall be accountable to the Ministry of Finance and Economic Development:

a) the Central Statistics Agency;
b) the Ethiopian Mapping Agency;
c) the Board of Trustee for Public Enterprises.

9/ The following executive organs shall be accountable to the Ministry of Revenue:

a) the Ethiopian Customs Authority;
b) the National Lottery administration.

10/ The Ethiopian Mine Action Office shall be accountable to the Ministry of Federal Affairs;

፲፩/ የሚከተሉት አስፈጻሚ አካላት ተጠሪነት ለጤና ጥበቃ ሚኒስቴር ይሆናል፣

ሀ) የኢትዮጵያ መድኃኒት አስተዳደርና ቁጥጥር ባለሥልጣን፣
ለ) የኤች.አይ.ቪ/ኤድስ መከላከያና መቆጣጠሪያ ጽሕፈት ቤት፡፡

፲፪/ የልዩ ዐቃቤ ሕግ ጽሕፈት ቤት ተጠሪነት ለፍትሕ ሚኒስቴር ይሆናል፡፡

፲፫/ የኢትዮጵያ የብሮድካስት ባለሥልጣን ተጠሪነት ለማስታወቂያ ሚኒስቴር ይሆናል፡፡

፲፬/ ብሔራዊ የሚቲዎሮሎጂ ኤጀንሲ ተጠሪነት ለውሃ ሀብት ሚኒስቴር ይሆናል፡፡

፲፭/ የሴቶች ልማት ፈንድ ጽሕፈት ቤት ተጠሪነት ለሴቶች ጉዳይ ሚኒስቴር ይሆናል፡፡

፲፮/ የሚከተሉት አስፈጻሚ አካላት ተጠሪነት ለባህልና ቱሪዝም ሚኒስቴር ይሆናል፣

ሀ) የቅርስ ጥናትና ጥበቃ ባለሥልጣን፣
ለ) የብሔራዊ ቤተመዛግብትና ቤተመጻሕፍት ኤጀንሲ፣
ሐ) ብሔራዊ ቲያትር፣
መ) የኢትዮጵያ የስብሰባ ማዕከል፡፡

፲፯/ የሚከተሉት አስፈጻሚ አካላት ተጠሪነት ለማዕድንና ኢነርጂ ሚኒስቴር ይሆናል፣

ሀ) የኢትዮጵያ ጂኦሎጂካል ሰርቬይ፣
ለ) የኢትዮጵያ የገጠር ኢነርጂ ልማትና ማስፋፊያ ማዕከል፡፡

፲፰/ የሚከተሉት አስፈጻሚ አካላት ተጠሪነት ለትራንስፖርትና መገናኛ ሚኒስቴር ይሆናል፣

ሀ/ የትራንስፖርት ባለሥልጣን፣
ለ/ የኢትዮጵያ ሲቪል አቪዬሽን ባለ ሥልጣን

## ክፍል አራት
## ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች

### ፴፬. የተሻሩ ሕጎች

፩/ የሚከተሉት ሕጎች በዚህ አዋጅ ተሽረዋል፣

11/ The following executive organs shall be accountable to the Ministry of Health:

a) the Ethiopian Drug Administration and Control Authority;
b) the HIV/AIDS Protection and Control Office.

12/ The Special Prosecutor’s Office shall be accountable to the Ministry of Justice.

13/ The Ethiopian Broadcasting Authority shall be accountable to the Ministry of Information.

14/ The National Meteorological Service Agency shall be accountable to the Ministry of Water Resources;

15/ Office of Women’s Development Fund shall be accountable to the Ministry of Women’s Affairs.

16/ The following executive organs shall be accountable to the Ministry of Culture and Tourism:

a) the Authority for Research and Conservation of Cultural Heritage;
b) the National archives and Library Agency;
c) the National Theatre;
d) the Ethiopian Conference Center.

17/ The following executive organs shall be accountable to the Ministry of Mines and Energy;
a) the Ethiopian Geological Survey;
b) the Ethiopian Rural Energy development and Promotion Center.

18/ The following executive organs shall be accountable to the Ministry of Transport and Communications:

a) the Transport Authority;
b) the Ethiopian Civil Aviation Authority.

## PART FOUR
## MISCELLANEOUS PROVISIONS

### 34. Repeal

1/ The following legislations are hereby repealed:

ሀ) የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ አስፈጻሚ አካላትን ሥልጣንና ተግባር ለመወሰን የወጣው አዋጅ ቁጥር ፬/፲፱፻፹፯ /እንደተሻሻለ/፣

ለ) የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ አስፈጻሚ አካላትን አደረ ጃጀት ለማሻሻል የወጣው አዋጅ ቁጥር ፪፻፶፮/፲፱፻፺፫ /እንደተሻሻለ/፣

ሐ) የቱሪዝም ኮሚሽን ማቋቋሚያ አዋጅ ቁጥር ፲፩/፲፱፻፹፯

መ) የመንግሥት ቤቶች ሽያጭ አስፈጻሚ ጽሕፈት ቤት ማቋቋሚያ አዋጅ ቁጥር ፩፻፲፪/፲፱፻፹፯

ሠ) የጤና አጠባበቅ ትምህርት ማዕከል ማቋቋሚያ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር ፵/፲፱፻፺፩::

፪/ ከዚህ አዋጅ ጋር የሚቃረን ማናቸውም ሕግ፣ ደንብ፣ መመሪያ ወይም የአሠራር ልምድ በዚህ አዋጅ በተመለከቱ ጉዳዮች ላይ ተፈጻሚነት አይኖረውም::

## ፴፭. መብትና ግዴታዎች ስለማስተላለፍ

፩/ የኮንስትራክሽንና የኢነርጂ ዘርፎችን ከሚመ ለከቱት በስተቀር የመሠረተ ልማት ሚኒስቴር መብትና ግዴታዎች በዚህ አዋጅ ለትራንስፖርትና መገናኛ ሚኒስቴር ተላልፈዋል::

፪/ የከተሞች ልማት ዘርፍን የሚመለከቱ የፌዴራል ጉዳዮች ሚኒስቴር መብትና ግዴታዎች እንዲሁም የኮንስትራክሽን ዘርፍን የሚመለከቱ የመሠረተ ልማት ሚኒስቴር መብትና ግዴታዎች በዚህ አዋጅ ለሥራና ከተማ ልማት ሚኒስቴር ተላልፈዋል::

፫/ በሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር ፵/፲፱፻፺፩ ተቋቁሞ የነበረው የጤና አጠባበቅ ትምህርት ማዕከል መብትና ግዴታዎች በዚህ አዋጅ ለጤና ጥበቃ ሚኒስቴር ተላልፈዋል::

፬/ የባህል ዘርፍን የሚመለከቱ የወጣቶች፣ የስፖርትና የባህል ሚኒስቴር መብትና ግዴታዎች እንዲሁም በአዋጅ ቁጥር ፲፩/፲፱፻፹፯ ተቋቁሞ የነበረው የቱሪዝም ኮሚሽን ግዴታዎች በዚህ አዋጅ ለባህልና ቱሪዝም ሚኒስቴር ተላልፈዋል::

a) the Definition of Powers and Duties of the Executive Organs of the Federal Democratic Republic of Ethiopia Proclamation No. 4/1995 (as amended);

b) the Reorganization of the Executive Organs of the Federal democratic Republic of Ethiopia Proclamation No. 256/2001 (as amended);

c) the Tourism Commission Establishment Proclamation, No. 11/1995;

d) The Office for the Sale of Government-owned Houses Establishment Proclamation No. 112/1995;

e) the Health Education Center establishment Council of Ministers Regulations No. 40/1998.

2/ No law, regulation, directive or practice shall, in so far as it is inconsistent with this Proclamation, have force or effect with respect to matters provided for by this Proclamation.

## 35. Transfer of Rights and Obligations

1/ The rights and obligations of the Ministry of Infrastructure, other than those relating to construction and energy sectors, are hereby transferred to the Ministry of Transport and Communications;

2/ The rights and obligations of the Ministry of Federal Affairs relating to urban development sector and the rights and obligations of the Ministry of Infrastructure relating to construction sector are hereby transferred to the Ministry of Works and Urban Development;

3/ The rights and obligations of the Health Education Center established under the Council of Ministers Regulations No. 40/1998 are hereby transferred to the Ministry of Health;

4/ The rights and obligations of the Ministry of Youth, Sports and Culture relating to the cultural sector and the rights and obligations of the Tourism Commission established under Proclamation No. 11/1995 are hereby transferred to the Ministry of Culture and Tourism.

፭/ የባህል ዘርፍን ከሚመለከቱት በስተቀር የወጣቶች፣ የስፖርትና የባህል ሚኒስቴር መብትና ግዴታዎች በዚህ አዋጅ ለወጣቶችና የስፖርት ሚኒስቴር ተላልፈዋል፡፡

፮/ የኢነርጂ ዘርፍን የሚመለከቱ የመሠረተ ልማት ሚኒስቴር መብትና ግዴታዎች በዚህ አዋጅ ለማዕድንና ኢነርጂ ሚኒስቴር ተላልፈዋል፡፡

፯/ በአዋጅ ቁጥር ፩፻፲፪/፲፱፻፺፭ ተቋቁሞ የነበረው የመንግሥት ቤቶች ሽያጭ አስፈጻሚ ጽሕፈት ቤት መብትና ግዴታዎች በዚህ አዋጅ ለኪራይ ቤቶች ኤጀንሲ ተላልፈዋል፡፡

## ፴፮. <u>አዋጁ የሚጸናበት ጊዜ</u>

ይህ አዋጅ ከጥቅምት ፩ ቀን ፲፱፻፺፰ ዓ.ም ጀምሮ የፀና ይሆናል፡፡

አዲስ አበባ ህዳር ፰ ቀን ፲፱፻፺፰ ዓ.ም

ግርማ ወልደጊዮርጊስ

የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ፕሬዚዳንት

5/ The rights and obligations of the Ministry of Youth, Sports and Culture other than those relating to the cultural sector are hereby transferred to the Ministry of Youth and Sports;

6/ The rights and obligations of the Ministry of Infrastructure relating to energy sector are hereby transferred to the Ministry Mines and Energy;

7/ The rights and obligations of the Office for the Sale of Government-Owned Houses established under Proclamation No. 112/1995 are hereby transferred to the Rented Houses Agency.

## 36. Effective Date

This Proclamation shall enter into force on the 11th day of October, 2005.

**Done at Addis Ababa, this 17th day of November, 2005**

**GIRMA WOLDEGIORGIS**

**PRESIDENT OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA**